
ምንዱባን
ከቪክቶር ሁጎ
ተርጓሚ፡- ዮሐንስ ገ/እግዚ


ኢትዮ - ትረካ
እንኳን ደና መጡ ! !
@ethio_terka
TAFT
PHOTOGRAPHY

# ምንዱባን

## (ሌይ ሚዘራብል)

ከቪክተር ህዩጎ

ትርጉም

ከዮሓንስ ገ/ጻድቕ

## ማውጫ


| ክፍል | ገጽ |
| --- | --- |
| አርእስት | |
| **ፋንቲን፡-** | |
| ከምዕራፍ አንድ - ምዕራፍ ሰባት | *5 - 109* |
| **ኮዜት፡-** | |
| ከምዕራፍ ስምንት - ምዕራፍ አሥራሁለት | *110- 162* |
| **ማርየስ፡-** | |
| ከምዕራፍ አሥራሶስት - ምዕራፍ አሥራሰባት | *163- 235* |
| **ቅዱስ ዴኒስና ከፕሉሜ ጎዳና ያለ ቤት፡-** | |
| ከምዕራፍ አሥራ ስምንት - ሃያ ስድስት | *236- 318* |
| **ዠን ቫልዠ፡-** | |
| ከምዕራፍ ሃያ ሰባት - ምዕራፍ ሰላሳአንድ | *319- 376* |



2ኛ እትም

እንደገና የማሳተም መብት የተርጓሚው ነው

*አዲስ አበባ - 2004 ዓ.ም.*

[illegible] ☎011-155 [illegible]


## መግቢያ

ይህ «ሌይ ሚዘራብል» የተባለው የቪክተር ሁጎ መጽሐፍ ለመተርጐም የተነሳሳሁት በውስጡ ብዙ የሕይወት ገጠመኞች ስላሉትና እነዚህም ገጠመኞች ትምህርት በመስጠት የሕይወት ምንነትን ያሳያሉ በሚል እምነት ነው:: ታሪኩ ውስጥ ለማመን የሚከብዱ ብዙ የሕይወት ገጠመኞች ቢኖሩም ሕይወት በአጋጣሚ የተሞላ ስለሆነ ገጠመኞቹ ከእውነት የራቁ ናቸው ብሉ ለመደምደም አይቻልም::

ፈረንሳዊው ሚስተር ሁጎ ይህን መጽሐፍ ከደረሰ በኋላ መጽሐፉን ለምን እንደጻፈው ሲጠየቅ «አዎን፣ የሰው ልጅ ለገሰሰቦች በጎ ፈቃድ እስከተተወ ድረስ በሰዎች ላይ የሚወሰነውን ለማፕፋት እመጣለሁ፣ ባርነትን እወገዛለሁ፣ ድህነትን እጠፋለሁ፣ ድንቁርናን ለማስወገድ እስተምራለሁ፣ የታመመን እከማለሁ፣ ጨለማ ተወግዶ ብርሃን እንዲሰፍን እፕራለሁ፣ ጥላቻን እጠላለሁ፣ እነነቴ ይህ ሲሆን 'ሌይ ሚዘራብልን' የጻፍኩትም ለዚሁ ነው» ሲል መልሶአል:: የእኔም እምነት ከዚህ የራቀ አይደለም::

ቪክተር ሁጎ ይህን መጽሐፍ ሲደርስ ዓላማው አንድን ታሪክ ለማቅረብ ብቻ አልነበረም:: በተጓዳኝ ትክክለኛ ፍርድ ለፍና የሰዎች እኩልነትና መብት መጠበቅ አስፈላጊነትም ለመግለጽ ነበር:: የሰው ልጅ ሕይወት መዳንት ያለበት ራሱ ባወጣው ሕግ ብቻ ሳይሆን በሕሊና ዳኝነትም ጥምር ሲሆን፣ ይህ ከሆነ አይልም የተሰየው ኅብረተሰብ ለመፍጠር እንደሚቻል ሁጎ በመጽሐፉ የሚያሳስብ ይመስላል:: የዓለም ሁለት ገጽታዎች ማለት ክፋትንና ደግነትን በማሳየት ከክፋት ደግነት እንደሚሻል በማስገንዘብ በተደጋጋሚ ጽፎአል:: ቴናድዩን የክፋት ቁንጮ፣ ዠን ቫልዣን ለሌሎች ብሉ የሚኖር የደግነት ምሳሌ እንደሆነ አድርጎ አቅርቦአቸዋል::

መጽሐፉ ውስጥ ፍራንክ ወይም ሱስ እየተባለ ብዙ ጊዜ ቀጠቅሷል:: በዚያን ጊዜ አምስት ፍራንክ ከሞላ ጎደል አንድ የአሜሪካን ብር ሲሆን ሃያ ሱስ ደግሞ አንድ ፍራንክ ነበር:: የተጠቀሱት ሌሎች አርፍራሬ ገንዘቦች ከዚህ በታች ናቸው:: በመጽሐፉ ውስጥ የተጠቀሱት ዓመተ ምህረቶች ደግሞ የአውሮጳውያን ዘመን አቆጣጠር ናቸው::

ሌላው ለአንባቢ መጠቀስ ያለበት ጉዳይ ደግሞ ለአስተረጎገመው ነው:: አተረጓገሙ የቃል በቃል ትርጉም ዓይነት አይደለም:: በመሠረቱ መጽሐፉ ከዛሬ አንድ መቶ ሰባ አምስት ዓመት በፊት የተደረሰ ሲሆን የተጻፈውም ለፈረንሳይ ኅብረተሰብ በመሆኑ ለፈረንሳዮዊ ብቻ ለሚገባ የሚሰጡ አሳቦች አሉበት:: ስለዚህ ከዚህ ውስጥ ለኢትዮጵያ አንባቢ አይሆኑም ብዬ የገመትኳቸውን ትቼያቸዋለሁ:: ሆኖም መጽሐፉ ሥረ-መሠረቱን እንዳይለቅ የተቻለኝን ሁሉ ሞክሬአለሁ::

የሐንስ ገ/ጻድቅ

# ፋንቲን

## ምዕራፍ አንድ

## ቀና ሰው

በ1815 መሴ. ቻርለስ ብየንቬኑ መሪል የሞንቴስ ሱር ሞንቴስ ሀገረ-ስብከት ጳጳስ ነበሩ፡፡ እድሜያቸው 75 ሲሆን የሞንቴስ ሱር ሞንቴስ ሀገረ-ስብከት ጳጳስ ሁነው የተሾሙት በ1806 ዓ.ም ነበር፡፡ ጳጳሱ ወደ ሀገረ-ስብከታቸው ሲመጡ እህታቸው ወ/ት ባፕቲስታን አብረዋቸው ነበር የመጡት፡፡ እህትዬዋ ምንም እንኳን ትዳር ባይዙም እድሜ የጠገቡ ሲሆኑ ወንድማቸውን በአሥር ዓመት ይበልጧቸዋል፡፡

ከጳጳሱ ቤት ውስጥ ሌላም ሴት ነበሩ፡፡ እኝህ ሴት የወ/ት ባፕቲስታን እኩያ ናቸው፡፡ ሴትዬዋ ወ/ሮ ማግልዋር ይባላሉ፡፡ ሴትዮዋህ ቀደም ሲል የሌላ ሰው አገልጋይ ሆነው ሠርተዋል፡፡ አሁን ደግሞ የወ/ት ባፕቲስታንና የጳጳሱ ቤት ጠባቂ ሁነው ተቀጥረው ይሠራሉ፡፡

ጳጳሱ ከሀገረ-ስብከታቸው እንደደረሱ በሀገሩ ደምብ መሠረት ከፊልድ ማርሻል ቀጥሎ ያለውን ሹመት ይሰጣቸዋል፡፡ የክፍለ ሀገሩ መሪና የማዘጋጃ ቤቱ ሹም ከቤታቸው ሄደው «እንኳን ደህና መጡ» በማለት እጅ ይነስዋቸዋል፡፡ አቡኑም በተራቸው ከዚያ ለተገኙ ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ቡራኬ ይሰጣሉ፡፡ የከተማው ሕዝብ በአጠቃላይ አዲስ የተሾሙለትን ጳጳስ ለማየት በጉጉት ሲጠባበቅ ነበር፡፡

የጳጳሱ ቤት ከአንድ ሆስፒታል አጠገብ ሲሆን ቤቱ እጅግ በጣም ሰፊና ያማረ ነው፡፡ ሆስፒታሉ ይገኝ የነበረው ከረባዳ ሥፍራ ላይ ሲሆን ግቢው እንደ ጳጳሱ ቤት አይሰፋም፡፡ ጳጳሱ ወደዚያ በሄዱ በሦስተኛው ቀን ሆስፒታሉን ይጎበኛሉ፡፡ ከጉብኝቱ በኋላ የሆስፒታሉ አስተዳዳሪ ከቤታቸው ድረስ መጥቶ እንዲያነጋግራቸው ይጋብዙታል፡፡ አስተዳዳሪው ከጳጳሱ ቤት ይሄዳል፡፡

በሆስፒታሉ ውስጥ «ስንት በሽተኞች አሉ?» ሲሉ አስተዳዳሪው ጠየቁ፡፡

«ሃያ ስድስት» ሲል መለሰላቸው፡፡

«ልክ እኔ እንደቆጠርኳቸው ናቸው፤ አልተሳሳትኩም» አሉ ጳጳሱ፡፡

ጳጳሱ የቤታቸውን አዳራሽ በዓይናቸው ቃኙ፡፡ አመለካከታቸው አዳራሹን በዓይነ-ሕሊናቸው የሚለኩና የሚያከፋፍሉ ይመስሉ ነበር፡፡

«ይህ ክፍል ብቻ ሃያ አልጋ ይይዛል» አሉ እርስ በራሳቸው ሲነጋገሩ፡፡

ከዚያም ድምፃቸውን ከፍ አድርገው የሚቀጥለውን ተናገሩ::

«ወዳጄ የምለውን አጢነህ ስማኝ:: እዚህ ቦታ አንድ ስህተት የተፈጸመ ይመስላል:: እናንተ አምስት ወይም ስድስት ጠባብ ክፍሎች ናቸው ያሏችሁ:: ከዚያ ውስጥ ሃያ ስድስት ሰዎች ይተኛሉ:: እኛ እዚህ ሦስት ሰዎች ብቻ ነን:: ያለው ቦታ ግን ስለሃምሳ ሰው የሚበቃ ነው:: ታዲያ ይህ የአደላደል ስህተት አይመስልህም? የእኔን ቤት አንተ ብትወስድ፤ የአንተን ደግሞ እኔ ብወስድ ይሻላል::»

በሚቀጥለው ቀን ሃያ ስድስቱ በሽተኞች ወደ ጳጳሱ ቤት ተዛወሩ:: ጳጳሱም ሆስፒታሉን ተረከቡ:: ወሬው በከተማው ተነዛ:: በጥቂት ቀናት ውስጥ የጳጳሱን በጎ ምግባር በመከተል ለበጎ ተግባር የሚውል እርዳታ ይጎርፍ ጀመር:: በየቀኑ ከጳጳሱ ቤት በር የሚያንኳኳ ሰው ቁጥር እየበዛ ሄደ:: ሆኖም የሚመጣው ሰው ሁሉ እርዳታ ለማድረግ ብቻ ሳይሆን ምፅዋት ለመቀበልም ነበር:: ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ጳጳሱ የብዙ ችግረኞች ቀላቢ፣ ምፅዋት ሰጪና ገንዘብ ሰብሳቢ ሆኑ:: ብዙ ገንዘብም ከጳጳሱ እጅ እየገባ ለድሃ ይሰጥ ጀመር:: የሚገኘው ገቢ ግን ልክ ከደረቀ አፈር ላይ እንደሚፈስ ውሃ ገና ከመገኘቱ ወጪ ሆኖ በቶሎ ያልቃል:: ጳጳሱ ገንዘብ ቢያገኙም ከተገኘው ገቢ ጥቂቱን እንኳን ለራሳቸው ወደጎን አላሉም:: እንዲያውም ከነአካቴው የራሳቸውንም ይዞ ይሄድ ጀመር:: ጳጳሳትን ከስማቸው አስቀድሞ ንጽህናቸውን ለማረጋገጥ ብፁዕ ወቅዱስ እያሉ መጥራት የተለመደ ቢሆንም በዚያ አካባቢ ይገኙ የነበሩት ነዳያን ፍቅራቸውንና ቅርበታቸውን ለመግለጽና የጳጳሱን ደግነት ለማውሳት ብፁዕ ወቅዱስ በማለት ፈንታ «አባ ደጉ» እያሉ ይጠሯቸዋል::

እኚህ ደግ ሰው በ1815 ዓ.ም ምንም እንኳን 75 ዓመት ቢሞላቸውም ከስልሣ ዓመት በላይ የሆናቸው አይመስሉም ነበር:: ቁመታቸው እጅግም ረጅም ሳይሆን መጠነኛ ሆኖ ሰውነታቸው ደልዳላ ነው:: ክብደታቸውን ለመቆጣጠር በእግር መሄድ ያዘወትራሉ:: ሲራመዱ መሬት በኃይል እየረገጡ ከወገባቸው ትንሽ ጎበጥ ይላሉ::

የልጅ ፈገግታ በተጎናጸፈ አንደበት ሲናገሩ ከግርማ ሞገሳቸው ብዛት የሰማቸው ሁሉ የመንፈስ እርካታን ያገኛል:: ከመላ ሰውነታቸው ደስታ የሚንፀባረቅ ይመስላል:: ደግነት የተቀረጸው አካላቸውና ወተት የመሰለው ጥርሳቸው ፈገግ ሲል እኚያ «ጨዋ ሰው፤ እድሜ የተቸረ ሽማግሌ፤ ደግ ሰው» በማለት ለደጋግ ሰዎች የምንሰጠው ትርጉም ሁሉ በእኚህ ሰው ላይ ጎልቶ ይታያል:: ለመጀመሪያ ጊዜ ላያቸው እንኳን ስለብቃታቸውና ስለደግነታቸው አይጠራጠርም:: ነገር ግን አንድ ሰው ለጥቂት ሰዓት ከጳጳሱ ጋር ቢቆይና በአሳብ ጥሞና ተውጠው ቢያያቸው ቀስ በቀስ መለያዎቻቸውን ይገነዘባል:: ግርማ ሞገሳቸው በቃላት ለመግለጽ በማይቻል ሁኔታ ያስፈራል:: ሰፊውና ክስታራው ፊታቸው እንዲሁም ሻሽ የመሰለው ፀጉራቸው ክብር የተጎናጸፈ ለመሆኑ በግልጽ ይታያል:: ግርማ ሞገስ ከውበታቸው እየፈለቀ ሲወጣ የሚያልቅ ቢመስልም የአንፀባራቂነት ኃይል እንዳለው አያጠራጥርም:: እንዲያውም አንድ ሰው ሁኔታቸውን በጥሞና ሲመለከት «አንድ መልአክ በፈገግታ አጊጦ ያየኛል» የሚል ስሜት ያድርበታል:: እኚህ ሰው የሚያሰላስሉት ስለ ክቡር ጉዳይ እንጂ ስለርካሽ ነገር ላለመሆኑ ጥርጣሬ አይገባውም::

ጸሎት ማድረስ፤ ምፅዋት መስጠት፤ የመንፈስ ስቃይ የደረሰበትን ማጽናናት፤ ወንድማማችነትን መስበክ፤ ራስን ለሌሎች መስዋዕት ማድረግ፤ በእምነት ራስን መግራት የጳጳሱ የእለት ተዕለት ኑሮ ሲሆን ይህም ኑሮ በበጎ አሳብ፤ በምርጥ ቃላትና በበጎ ተግባር የተሞላ ነበር::

ክረምት ይሁን በጋ ሁለቱ ሴቶች ሲተኙ ብውስንታቸው ወደ ጓሮ ሄደው አትክልት ውስጥ ለአንድ ወይም ለሁለት ሰዓት ፈጣሪያቸውን በማሰብ ከዚያ ካልቆዩ ኑሮአቸው የተሟላ አይመስላቸውም:: አሳባቸውን ሰብስበውና የመንፈስ እርጋታን አግኝተው የምሽቱን ሰላምና ፀጥታ ከሰማይ የመንፈስ እርካታ ጋር እያነፃፀሩ የከዋክብትን ብዛት በመመልከት ከአትክልቱ ውስጥ ይንሸራሸራሉ::

በዚያች ሰዓት አበቦች ያለመስገብገብ የሚለግሱትን መልካም መዓዛ እየማጉ ጥቅጥቅ ካለ ጨለማ ውስጥ እንደበራ ሻማ ብቻቸውን በፍጥረታት መካከል በደስታ የተዋበው ነፍሳቸውን ዘርግተው ይቆማሉ:: አእምሮአቸው ውስጥ ምን እንዳለ ራሳቸውን ቢጠይቁ መልሱን አያውቁትም:: ሆኖም ከሰውነታቸው ውስጥ አንድ ነገር ወጥቶ እንደሚሄድና አንድ ነገር ደግሞ ከሰውነታቸው ላይ እንደሚያርፍ ይሰማቸዋል፤ አንድ ዓይነት ምሥጢር መከናወኑን ይገነዘባሉ::

እኚህ እድሜ የጠገቡና ፈጣሪያቸውን የቀረቡ ሰው የእረፍት ጊዜያቸውን የሚያጠፉት ቀን ቀን አትክልት በመኰትኰት ሲሆን ማታ ማታ ደግሞ ፈጣሪያቸውን በጸሎት በማመስገን ስለሆነ ሌላ የሚፈልጉት ነገር አልነበረም:: ምድሩ በአበባ፣ ሰማዩ በከዋክብት በማጌጡ የመንፈስ እርካታ ይሰጣቸዋል::

# ምዕራፍ ሁለት

## ወድቀት

ጊዜው 1815 ዓ.ም ወሩ ጥቅምት ነው:: በሐይዋ ልትጠልቅ አንድ ሰዓት ያህል ሲቀራት አንድ በእግሩ የሚጓዝ ሰው ወደ ሞንቴስ ሱር ሞንቴስ ትንሺቱ ከተማ ይገባል:: በየመስኮቶቻቸውና በየቢሮዎቻቸው አጠገብ የቆሙ ጥቂት ሰዎች ይህን መንገደኛ ይጠራጠሩታል:: ሆኖም ከእርሱም ይበልጥ የተሰቃየ ሌላ ሰው ለማግኘት እንደማይቻል ፊቱ ይመሰክራል:: ቁመቱ መካከለኛና አጥንተ-ወፍራም ሲሆን የሰውነቱ አፈጣጠር ግዙፍ ነው:: በእድሜው ሙሉ ሰው ይመስላል:: ምናልባት አርባ ስድስት ወይም አርባ ሰባት ዓመት ሳይሆነው አይቀርም:: የፀሐይ ጨፈር[1] ነፋስና ከሰውነቱ የወጣው ላብ ያጠቆረውና ያንገላታው ቆብ ግማሽ ፊቱን ሸፍኖበታል:: ቀደም ሲል የፈሰሰው ላብ ከፊቱ ላይ ደርቆ አዲስ ደግሞ ከፊቱ ላይ ሲወርድ ድካሙን በግልጽ ያሳያል:: የለበሰው ሸካራና ቢጫ ሸሚዝ ከዘዙ-በታ ላይ በመቦጫጨቁ የደረቱን አጥንት ለፀሐይ ዳርጎታል:: ሸሚዙ በነፋስ ኃይል እንዳይሄድ ሳይሆን አይቀርም ከረባትና አሮጌ መስቀል በተንጠለጠለበት ገመድ አሲሮታል:: የተቀዳደደ ሰማያዊ ሱሪ ታጥቋል:: ሱሪው አንደኛው ጉልበቱ ላይ ሳስቶ ሲነጣ ሌላው ላይ ተቀዳድዶአል:: ከአንድ ጎኑ ላይ አረንጓዴ ጨርቅ የተጣፈበትና ግራጫ መልክ ያለው አሮጌ ሰደርያ ደግሞ ደርቦአል:: በምናምን የተሞላ አዲስ አቁማዳ በዱላ በማያያዝ በጀርባው አንጠልጥሎአል:: በእጁ ደግሞ ሌላ ባለትልቅ ቋር ዱላ ይዟል:: የተንሻፈፈና ከጎኑ የተቀደደ አሮጌ ጫማ ያለካልሲ አጥልቆአል:: ፀጉሩን ተላጭቶት የበቀለ ሲሆን ጢሙ ግን በኃይል አድጓል:: ላቡና የሰውነቱ መዛል በእግር ብዙ መጓዙን ያረጋግጣል:: ከላዩ ላይ የሰፈረው አዋራ ለሰውዬው መጎሳቆል ሌላው ማስረጃ ነው::

ይህ ሰው ወደ ከተማው እንደገባ ወደ ግራ ታጥፎ ወደ ማዘጋጃ ቤት ያመራል:: ከዚያም ከማዘጋጃ ቤት ሹም ቢሮ ገብቶ ከሩብ ሰዓት በኋላ ከቢሮው ይወጣል::

በከተማው ውስጥ ጥሩ ማረፊያ ቤት ነበር:: መንገደኛው ወደዚያች ማረፊያ ቤት ሄደ:: ማረፊያ ቤቱ በከተማው የታወቀና ምርጥ የተባለ ነበር:: በቀጥታ ወደ ወጥ ቤት ሄደ:: የወጥ ቤቱ የጓሮ በር ወደ ዋናው ጎዳና የሚያስወጣ ሲሆን መንገደኛው የገባው በዚህ በኩል ነበር:: ወጥ ቤቱ ውስጥ ከአብዛኞቹ ምድጃዎች ላይ እንጨት በኃይል ተያይዞ እሳቱ ይንቦገቦጋል:: የወጥ ቤቱ ኃላፊ እሳቱ ከሚነድበት በቅኩላ እየተራመደ ሄዶ



የምግቡን ሁኔታ ይቃኛል:: የምግቡን መዳረስ የሚጠብቁ ሌሎች መንገደኞች ተሰብስበው ከነበረው ክፍል ውስጥ ሲስቁና ሲንጫጩ ይሰማል:: የሚዘጋጀው ምግብ መልክም ታና፤ እንኳን ለሚቀምሰውና ለሚያሸተተው ይቅርና መንገደኛውን ክፉኛ የሚጠራ ዓይነት ስለነበር እንግዶቹ ምን ዓይነት ሰዎች እንደነበሩ ለመገመት አያዳግትም::

የወጥ ቤቱ ኃላፊ በር ሲከፈት ሰምቶ እንግዳ መግባቱን ስለተገነዘበ አንገቱን ቀና ሳያደርግ «ጌታዬ ምን ይፈልጋሉ?» ሲል ይጠይቃል::

«የሚላስ፤ የሚቀመስና ማደሪያ ነው የምፈልገው» ይላል እንግዳው::

«ከዚህ የቀለለ ምን ነገር አለ!» ብሎ ኃላፊው ከተናገረ በኋላ አንገቱን ቀና አድርጎ ባይተዋሩን በመመልከት «ግን ይከፈላል» ይለዋል:: ሰውዬው ከኪሱ ውስጥ ትልቅ ቦርሳ አውጥቶ «ገንዘብ አለኝ» ሲል መለሰለት::

«እንግዲያውስ» አለ አስተናጋጁ፤ «ምን ልታዘዝ?»

ሰውዬው ቦርሳውን መልሶ ከኪሱ ውስጥ ከተተ:: ስልቻውን ከጫንቃው ላይ አውርዶ ከመሬት ላይ ወረወረው:: ዱላውን እንደያዘ እሳቱ አጠገብ ከነበረው ወንበር ላይ ቁጭ አለ:: ከተማው የተሠራው ከተራራ ጫፍ ላይ በመሆኑና ወሩም ጥቅምት ስለነበር የአካባቢው አየር በጣም ቀዝቃዛ ነበር::

የቤቱ ባለቤት ወዲህና ወዲያ ባለ ቁጥር መንገደኛውን አተኩሮ ይመለከተዋል::

«ምግብ ደርሷል?» ሲል መንገደኛው ጠየቀ::

«ተቃርቧል» አለ ኃላፊው::

እንግዳው ጀርባውን ለእሳት ሰጥቶ ሲሞቅ የሆቴሉ ባለቤት ቁራጭ እርሳስ ከኪሱ ካወጣ በኋላ ከመስኮት አጠገብ ከነበረው አነስተኛ ጠረጴዛ ላይ ተቀምጦ ከነበረው የማስታወሻ ደብተር አንዲት ቅጠል ቀደደ:: ምናምን ጻጽፎ ወረቀቱን በአቅራቢያው ለነበረውና እንደ ተላላኪም! እንደ ቤት ጠራጊም ይሠራ ለነበረው ልጅ ሰጠው:: የሆነ ነገር በጆሮው ለልጁ ሹክ ካለው በኋላ ልጁ ወደ ማዘጋጃ ቤት ሹም ቢሮ እትጣጫ ይሮጣል:: ይህ ሲሆን ግን መንገደኛው አላየም::

«እራት ደርሷል?» ሲል ለሁለተኛ ጊዜ ጠየቀ::

«አዎን ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ማቅረብ እንጀምራለን» አለ የቤቱ ጌታ::

ልጁ ወረቀቱን በእጁ እንደያዘ ተመለሰ:: የሆቴሉ ባለቤት ቸኩሎ አስቸኳይ መልስ ለመስማት እንደሚጓጓ ሰው ሁሉ የተጣጠፈውን ወረቀት

ከፈተ። በጥሞና ማንበብ ጀመረ። ከዚያም በአንድ እጁ አገጩን ደገፍ እንደማሰብ አለ። በሐሳብ ባህር የተዋጠ ወደሚመስለው መንገደኛ ተጠጋ።

«ጌታዬ» አለ፤ «ሊረዳዎት ባለመቻሌ አዝናለሁ። ያልተያዘ ክፍል ያለ መስሎኝ ነበር፤ ግን የለም።»

«ታዲያ» አለ መንገደኛው «ለአልጋ እንኳን ባይኖር የትም ቢሆን ሳር ተነዝንዞልኝ ልተኛ! ለማንኛውም ከእራት በኋላ እንወያይበታለን።»

«እራትም ልሰጥዎት አልችልም።»

መንገደኛው ይህን ሲሰማ «ይህስ ለነገር ነው» ይላል። ከተቀመጠበት ብድግ አለ።

«እህ... እህህ፤ ታዲያ እኔ እኮ በጣም ስለራበኝ ጠኔ ይዞኛል።»

«ምንም የለኝም» አለ የሆቴሉ ጌታ።

ሰውዬው ሳቁን ለቀቀው። ወደ እሳት ማንደጃው ዞር ብሎ የተጣደውን ምግብ ሁሉ ተመለከተ።

«ምንም የለኝም! ያ ሁሉ ምግብ እያለ!»

«ያ ሁሉ ምግብ ለሌላ ሰው ነው የተዘጋጀው።

ሰውዬው እንደገና ቁጭ አለ። ድምፁን ገቱ አድርጎ «ሆቴል ቤት ውስጥ ነው ያለሁት፤ ተርቤአለሁ፤ እኔ ደግሞ እዚሁ ነው የማድረው» አለ።

የሆቴሉ ባለቤት አንገቱን ገቱ አድርጎ ንዴት እየተናነቀው «ሰውዬ ውጣ» ይላል።

መንገደኛው ወደሚነደው እሳት ጠጋ ብሎ ትርኳሽ እንጨቶችን በያዘው ዱላ ወደ እሳቱ ረመጥ እያስጠጋ ሳለ «ውጣ» የሚል ቃል ሲሰማ መልስ ለመስጠት ፊቱን ያዞራል። የሆቴሉ ጌታ አፍጥጦ እያየው ለመናገር እድል ሳይሰጠው «ቢበቃን ይሻላል፤ በመጀመሪያ ማንንም ቢሆን በትህትና ማናገር ልማዴ ነው፤ ሰውዬ ያለ ጭቅጭቅ መንገድህን ብትቀጥል ይሻልሃል» ይለዋል።

ሰውየውን እጅ ከነሳ በኋላ ስልቻውን ተሸክሞ ከቤቱ ወጥቶ ሄደ።

ሰውራ ጎዳናውን ይዞ ወዴት እንደሚሄድ ሳያውቅ የሀፍረት ሸማውን ተከናንቦ እንደ ለዘነተኛና እንደተዋረደ ሰው እየተሸማቀቀ ጉዞውን ቀጠለ። ያስጠጉኝ እንደሆን በማለት የየቤቱን በር አንኳኳ። ግባ የሚለው ቢያጣ ፊቱን ሳይመልስ ቀጥ ብሎ ወደፊት ተጓዘ። ከሆቴል ቤቱ ቢመለስ ኖሮ



የሆቴሉ ባለቤት እዚያ ቤት ውስጥ ከነበሩት እንግዶችና ከተሳላፊ መንገደኞች ጋር ቆሞ በጣቱ እየጠቆመ ስለእርሱ በጉጉት ሲያወራቸው ያይ ነበር። ቢያያቸው ኖሮ ደግሞ የእርሱ ወደዚያ መምጣት የከተማው ወሬ እንደሚሆን ከሁናቴያቸውና ከአመለካከታቸው ሊገምት ይችል ነበር።

ይህ ሁሉ ሲሆን ግን መንገደኛው አላየም። ከችግር ማጥ ውስጥ የሚዋትቱ ሰዎች ወደኋላ መለስ ብለው አይመለከቱም፤ ሰንካላ እድል እንደሚከተላቸው ያውቃሉና። ከአውራ ጎዳናው ሳይወጣ ለጥቂት ጊዜ እንደተጓዘ ከማያውቀው ሰፈር ደረሰ። በሀዘን የተዋጠና የተከፋ ሰው ድካም እንደማይሰማው ሁሉ ድካሙ አልተሰማውም። ግን በድንገት ረሃብ ሞረሞረው። ሐሞቱ ሲንሰፈሰፍ ተሰማው። ምሽት ተቃርቧል።

ከተባረረበት ሆቴል ቤት ጀምሮ ከወደኋላው ይከተሉት የነበሩት ሕፃናት ድንጋይ ወረወሩበት። በቁጣ ወደ እነርሱ ዞሮ በያዘው ዱላ ሲያስፈራራቸው እንደ ወፍ መንጋ ተበተኑ። የእስር ቤት በራፍ እንዳለፈ ከደወል ጋር ተያይዞ ከበር ላይ የተንጠለጠለ የብረት ሰንሰለት አየ። መለስ ብሎ ደወሉን ደወለው። በሩ ተከፈተ።

«ጌቶች» አለ ቆቡን አውልቆ በትህትና እጅ እየነሳ፤ «ለማሬ ብቻ ከዚህ ያሳድሩኛል?»

«እስር ቤት ሆቴል ቤት አይደለም፤ ወንጀል ሠርተህ ከመጣህ በሩን እንከፍትልሃለን» አለ አንድ ድምፅ ከሩቅ። በሩ ተመልሶ ተዘጋበት። የዘበኞች ኃላፊ ነበር የተናገረው፡

ጊዜው እየመሸ ነው። ቀዝቃዛ አየር ከተራራው ወደ ነበረበት ሰፈር ይነፍሳል። እግሩ እየከበደው ቢሄድም መራመዱን ቀጠለ። ከከተማው ትንሽ ወጣ ሲል ለማደሪያ የሚሆነው የትልቅ ዛፍ ከለላ ወይም የተከመረ ድርቆሽ እንደሚያገኝ ተስፋ አደረገ። አንገቱን አቀርቅሮ ጉዞውን ተያያዘው። ሰው ከሚኖርበት አካባቢ የወጣ ስለመሰለው አንገቱን ቀና አድርጎ አካባቢውን በዓይኑ ቃኘ። ከእርሻ ሜዳ ደርሷል። ከፊት ለፊቱ ከሚገኘው ጉብታ ላይ የነበረው እህል ታጭዶ የሚታየው ቀረጡ ገለባ ብቻ ነው። አካባቢው በአጠቃላይ የተላጨ ፀጉር መስሎአል። ሰማዩ ጨልሞ ደመና ዞሮበታል። የደመናው ብዛት በአካባቢው ከሚገኙት ኮረብታ ላይ ያረፈ አስመስሎታል። ሆኖም ከአንዳንድ ሥፍራ የሚታዩት ከዋክብት ነፋስ ይዞት እንደሚሄድ ኩራዝ ደፋ ቀና ይላሉ። ጨረቃዋም ሳሳ ካለው ደመና ላይ ነጭ መስመር የዘረጋች ይመስል ብልጭ ድርግም ትላለች። አልፎ አልፎ መስመሩን የሚዘረጋው ጨረቃና ደፋ ቀና የሚሉት ከዋክብት አካባቢው ጨርሶ ጨለማ እንዳይሆን ረድተዋል። ስለዚህ የመሬቱን የሰማዩን ያህል

አልጨለሰመም:: ሆኖም አካባቢው በጣም ያስፈራል::

ከጉብታውና ከተንጣለለው ሜዳ ላይ ከአንድ ቅርጽ-ቢስ ዛፍ ሌላ ምንም አልነበረም:: ዛፉ መንገደኛው ከደረሰበት ሩቅ አልነበረም:: ሁናቴው ስላላማረው መንገደኛው ወደመጣበት ተመለሰ::

ከምሽቱ ወደ ሁለት ሰዓት ገደማ ሆኖአል:: አካባቢውን ስለማያውቅ መንገድ እንደመራው ብቻ ዝም ብሎ ተጓዘ:: የከንቲባውን ቤት እንዳለፈ ከትምህርት ቤት አካባቢ ደረሰ:: ትምህርት ቤቱን አልፎ እንደ ሄደ ቤተክርስቲያን አጋጠመው:: ገና ቤተክርስቲያኑን ሲያይ እጁን ጨብጦ ዓይኑን ወደላይ አንጋጠጠ::

ከቤተክርስቲያኑ ፊት ለፊት አንድ ማተሚያ ቤት አለ:: ሰውዬው ድካም አወራጭቶት ስለነበር ከዚህ የተሻለ ሥፍራ ሳይፈልግ ከማተሚያ ቤቱ አጠገብ ከነበረው የድንጋይ አግዳሚ መቀመጫ ላይ ተጋደመ::

ወዲያው እንደተጋደመ አንዲት አሮጊት ከቤተክርስቲያኑ ወጡ:: «ወዳጄ ከዚህ ምን ታደርጋለህ?» ሲሉ ጠየቁት::

«እየሽ የእኔ እማኝ፣ መተኛቴ ነዋ!» አለ በቁጣና በድፍረት የማይሆን መልስ መስጠቱ ሳይታወቀው:: ክብር የሚገባቸው እማኝዋና ደግዋ ሴት ማዳም ላ ማርኪዚ ይባላሉ::

«እንዴ! ከድንጋይ ላይ!» አሉ፤ «ሌሊቱን በሙሉ ከድንጋይ ላይ ተኝተህ ሊነጋልህ አይችልም:: ረሃብ እንዳንገላታህና ብርድ እንዳጠቃህ ሰውነትህ ይመሰክራል:: የሚያስጠጋ አላገኘህም?»

«ብዙ ቤት ሞከርኩ፤ የየቤቱን ደጃፍ አንኳኳሁ::»

«እና!»

«ሁሉም ሰው ከበራፌ ሂድ አለኝ::»

ደግዋ ሴት የሰውዬውን ጀርባ እየመቱ ከአደባባዩ ባሻገር የሚታየውንና ከጳጳሱ ቤት አጠገብ የነበረውን ቤት ጠቆሙት::

«ያንን ቤት ሞክረሃል?» ሲሉ ጠየቁት::

«አዎን::»

«ከዚያ ማዶ ከሚታየው ቤት አንኳኩተሃል?»

«የለም::»

«እዚያ ሞክር እስቲ::»

❀❀❀



## ፪

እንዲያ ደጉ ጳጳስ ከተማ ውስጥ ሲዘዋወሩ በመቆየታቸው ስለደከማቸው ያን እለት ማታ ከቢሮአቸው ሳይወጡ ብዙ ቆዩ:: በተጨማሪም ብዙ ሥራ በስንበራቸው «ሥራዬን ሳልጨርስ አልነሳም» በማለት ከእዚያው አመሹ::

ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ሲሆን እዚያው ሥራቸው ላይ ነበሩ:: በብዛት ወረቀትና በማስታወሻ ደብተር ላይ ጉልበታቸውን እያስደገፉ ሲጽፉ እንደተሰመደው እሊጋቸው አጠገብ ከነበረው ቡፌ ከብር የተሠራ ሳህን ለማውጣት መዳም ማግሎዋር ይገባሉ:: ሴትዩዋ ከተመለሱ በኋላ ጥቂት ቆይቶ ገበታ እንደቀረበና እህታቸው እንደሚጠብቋቸው በመንገር ጳጳሱ ወደ ምግብ ቤት ሄዱ:: ምግብ ቤቱ የአራት ማዕዘን ቅርጽ ያለው ዓይነት ሆኖ የእሳት ማንደጃ አለው:: ቢፈለግ ወደ አውራ ጎዳናው የሚያስወጣ በርም አለው:: በአትክልቱ በኩል መስኮት አለ::

መዳም ማግሎዋር ገበታውን ሠርተው ከጨረሱ በኋላ ጠረጴዛውን እያስተካከሉ ከመድምዋዜል ባፕቲስቲን ጋር ይጫወታሉ:: ገበታው አጠገብ ሻማ ከትንሽ ጠረጴዛ ላይ ተቀምጦ እየተቀጣጠለ ነው:: ከማንደጃው ውስጥ የተቀጣጠለው እሳት ፍም ብዛት ስለነበረው ክፍሉ ይሞቃል:: የቤታቸው በር እንዴት መቆለፍ እንዳለበት መዳም ማግሎዋር ሲያወሩ ጳጳሱ ይገባሉ::

መዳም ማግሎዋር ለእራት የሚሆን ሽቀጣሽቀጥ ለመግዛት ወደ ገበያ ሄደው ሳለ አንድ መግቢያ ያጣ ማጅራት መቺ ከተማ መግባቱንና ይህ ሰው በጊዜ ከቤታቸው በማይገቡ ሰዎች ላይ አደጋ ሊያደርስ እንደሚችል ሲወራ ይሰማሉ:: ሁለቱ ሴቶች ስለዚሁ ጉዳይ ሲያወሩ ጳጳሱ ስለገቡ «አባታችን መዳም ማግሎዋር የሚናገሩትን ይሰማሉ?» በማለት ጠየቋቸው::

«የምትሉት ነገር ግልጽ ባይሆንልኝም ሰምቼአለሁ» አሉ ጳጳሱ:: ከዚያም ፊታቸውን ወደሚነድደው እሳት በማዞርና እጆቻቸውን ከጉልበታቸው ላይ በማሳረፍ ሠራተኛቸውን እያዩ «ታዲያስ፣ ምንድነው ጉዳዩ? የሚያስፈራ ነገር አለ እንዴ?» ሲሉ ጠየቁ::

ይህን ጊዜ መዳም ማግሎዋር ሳያስቡት ታሪኩን በማጋነን አዋሯቸው:: «ያለመጠለያ ባዶ እግሩን የሚጓዝ ማጅራት መቺ፣ ሌባ፣ ቀማኛ ከተማ ገብቷል» አሉ:: «ከዋየን ባቡር ሄዶ ማረፊያ በጠየቀ ባለቤቱ አልፈቀደለትም:: ከመሸ በኋላ ከተማ ውስጥ ሲዘዋወር ታይቷል:: ስልቻውን በገመድ አስሮና ተሸክሞ ይዞራል:: መልኩ ደግሞ በጣም የሚያስፈራ ነው::»

«እውነትግን ነው?» ሲሉ ጳጳሱ ጠየቁ::

ጳጳሱ በታሪኩ የተመሰጡና ፍርሃትም ያደረባቸው ስለመሰላቸው

መዳም ማግልዋር ታሪካቸውን በኩራት ይቀጥላሉ፡፡ «እምን አባቶችን፤ እውነት ነው፡፡ ዛሬ ማታ ከተማ ውስጥ አንድ ነገር ይሆናል፡፡ ከተማው ሁሉ ይህንኑ ነው የሚያወራው፡፡ መድምዋዜል ባፕቲስታን ደግሞ እንደምትሰው...» በማለት ሴትዮዋ ንግግርዋን ስትቀጥል «እኔ» በማለት የጳጳሱ እህት ጣልቃ ገብተው «ያልኩት ነገር የለም» ይላሉ፡፡

ተቃውሞውን እንዳልሰሙ መስለው መዳም ማግልዋር ልፍለፋቸውን ቀጠሉ፡፡

«የዚህ ቤት ደህንነት ይህን ያህል አስተማማኝ አይደለም፡፡ አባታችን ቢፈቅዱልኝ ሄጄ ቁልፍ ለሚሠሩት ሰውዬ የድሮዎቹን መቀርቀሪያዎች መልሰው እንዲገጥሟቸው ልንገራቸው፡፡ መቀርቀሪያዎቹ ስላሉ በደቂቃ ይሰርዋቸዋል፡፡ ለዛሬ ማታ ብቻ እንኳን ባይሆን ለወደፊቱም ጥሩ ነው፤ በራችን ጠንካራ መቀርቀሪያ ይግባለት፡፡ በቀላሉ የሚከፈት በር እጅግ አደገኛና አስፈሪ ነው፡፡ አባታችን እንደሆን ይቅርታ ቢደረግልኝ እኩለ ሌሊት እንኳን ቢሆን ቤት ለእንግዳ፤ ይግቡ የማለት ልምድ አለብዎት፡፡ ግን.. መቼም ለዚህ ፈቃድ መጠየቅ እንኳን አስፈላጊ...» ሴትዮዋ አሳባቸውን ሳያጠቃልሉ በር በኃይል ይንኳኳል፡፡ «ይግቡ» አሉ ጳጳሱ፡፡

በሩ ተከፈተ፡፡ አንድ ሰው ሰዎቹ ከነበሩበት ክፍል ውስጥ ገባ፡፡

ያ የምናውቀው ማደሪያ ፍለጋ ከቤት ቤት፤ ከሥፍራ ሥፍራ ይንከራተት የነበረው መንገደኛ ነበር፡፡ ሰውዬው በሩን መልሶ ሳይዘጋ አንድ እርምጃ ወደፊት ተራምዶ ቆም አለ፡፡ ስልቻውን በጀርባው ተሸክሞ ዱላውን በእጁ እንደያዘ ነው፡፡ የእሳቱ ውጋጋን ከፊቱ ላይ ሲያርፍ ሸካራውና ድካም ያጎሳቆለው ፊቱ የጭካኔ ምልክት እንዳለበት አጉልቶታል፡፡ ሆኖም ያ ስሜት ወደ ውስጥ የተቀበረ እንጂ በግልጽ የወጣ አልነበረም፡፡ የመናፍስት በአካል መታየት ነበር የሚመስለው፡፡

መዳም ማግልዋር ለመጮህ እንኳን አቅም አልነበራቸውም፡፡ እንደቆሙ እየተንቀጠቀጡ አፋቸውን ከፍተው ቀሩ፡፡

መድምዋዜል ባፕቲስታን ዞር ሲሉ ሰውዬው ወደ ውስጥ ሲገባ አዩ፡፡ በፍርሃት ተውጠው ከመቀመጫቸው ብድግ አሉ፡፡ ከዚያም ዝግ ብለው ወደሚነድደው እሳት ዞረው ወንድማቸውን ተመለከቱ፡፡ ፊታቸውን ሲያዩ ትንሽ መንፈሳቸው ተረጋጋ፡፡

ጳጳሱ ሰውዬውን በጥሞና ተመለከቱት፡፡ ምን እንደሚፈልግ ሊጠይቁት አፋቸውን እንደከፈቱ ለመናገር እድል ሳይሰጣቸው የያዘውን ዱላ በሁለት እጁ በመመርኮዝ ከዚያ የነበሩትን ሰዎች አንድ በአንድ ካቶን በኋላ ድምፁን ከፍ አድርጎ መናገር ጀመረ፡፡



«ተመልከቱኝ! ስሜ ዣን ቫልዣ ይባላል፡፡ የተፈረደብኝ ወንጀለኛ ነኝ፡፡ ለአሥራ ዘጠኝ ዓመት እሥር ቤት ነበርኩ፡፡ ከአራት ቀን በፊት ተፈታሁ፡፡ ወደ ፓንታልዬ ነው የምሄደው፡፡ የተፈታሁ እለት ከቱሉን ተነስቼ በእግሬ እየተጓዝኩ ዛሬ ከእዚህ ደርሻለሁ፡፡ በዛሬው ቀን ብቻ ወደ 55 ኪሎ ሜትር ያህል ተጉዤአለሁ፡፡ ማምሻውን ወደዚህ ከተማ እንደገባሁ ወደ ሆቴል ቤት ሄጄ ማደሪያ እንዲሰጡኝ ጠየቅሁ፡፡ ከእሥር ቤት የተሰጠኝ መታወቂያ ብቻ በመያዜ ከዚያ ላድር አልቻልኩም፡፡ ወህኒ ቤት ሄጄ እንዲያሳድሩኝ ብጠይቃቸው ከእዚያም አባረሩኝ፡፡ ከከተማ ወጣ ብዬ ከዛፍ ስር ለማደር ፈልጌ ነበር፡፡ ሆኖም ጨለማውን ፈራሁት፡፡ ደመናውም ስላንዣበበ ይዘንባል ብዬ ስለሰጋሁና ደግ አምላክ ኖሮም ዝናቡን ያቆማል ብዬ ስላላመንሁ መጠጊያ አገኛለሁ በማለት ወደዚች ከተማ ተመለስኩ፡፡ ከከተማው መካከል ከቤተክርስቲያኑ ፊት ለፊት ከድንጋይ ላይ ተጋደምኩ፡፡ እንደተጋደምኩ አንዲት ደግ ሴት ቤታችሁን ጠቁማ ከእዚያ ቤት አንኳኳ አለችኝ፡፡ መጥቼም አንኳኳሁ፡፡ ይህ ቤት የማን ቤት እንደሆነ ብትነግሩኝ፡፡ ሆቴል ቤት ነው? ከሆነ ገንዘብ አለኝ፡፡ እሥር ቤት ውስጥ አሥራ ዘጠኝ ዓመት ሠርቼ 109 ፍራንክና 15 ሱስ ያህል አጠራቅሜአለሁና ሂሣቡን እከፍላለሁ፡፡ በጣም ደክሞኛል፡፡ 55 ኪሎሜትር በአንድ ቀን በእግር መጓዝ ማለት ምን ያህል አድካሚ እንደሆነ ሳትገነዘቡ አትቀሩም፡፡ ደግሞም በጣም ርቦኛል፡፡ ታሳድሩኛላችሁ?»

«መዳም ማግልዋር» አሉ ጳጳሱ፤ «ሌላ ሳህን አምጪ፡፡»

ሰውዬው ጥቂት ራመድ ብሎ ከጠረጴዛው ላይ ተቀምጦ ይነድ ወደነበረው የሻማ መብራት ጠጋ አለ፡፡ ሰዎቹ ችግሩን ያላወቁለት ስለመሰለው «ቆዩ» ሲል ሎክ ብሎ በቁጣ ከተናገረ በኋላ «እሱን አይደለም የምለው፤ ተግባብተናል? የመርከብ ቀዛፊ ባሪያ፤ ወንጀለኛ ነኝ፡፡ ያንን አድካሚ የመቅዘፍ ሥራ ስሠራ ኖሬ ነው የምመጣው፡፡ መታወቂያዬን ተመልከቱ፡፡ የወንጀለኛ መታወቂያ ነው፡፡ ሌላ መታወቂያ ስለሌለኝ የትም ብሄድ ያባርሩኛል፡፡ ውሰዱት! ሰው ሁሉ እንደሆነ አባርሮኛል፡፡ እናንተስ ትቀበሉኛላችሁ? ይህ ቤት ለመሆኑ ሆቴል ቤት ነው? የምቀምሰው ነገር ትሰጡኛላችሁ? ማደሪያስ ትፈልጉልኛላችሁ? የፈረሶች ጋጣ እንኳን ቢሆን አልጠየፍም፡፡»

«ማዳም ማግልዋር አሉ ጳጳሱ፤ «ከእኔ መኝታ ቤት አጠገብ ካለው ክፍል ውስጥ ያለው አልጋ ይነጠፍ፡፡»

ማዳም ማግልዋር ትእዛዙን ለመፈጸም ወጡ፡፡ ጳጳሱ ፊታቸውን ወደ እንግዳው አዞሩ፡፡

«ልጄ አረፍ በልና ሰውነትህን አሟሙቅ፡፡ በቶሎ ገበታ እንቀርባለን፡፡

እራታችንንም እስክንበላ መኝታው ይዘጋጅልሃል::»

በመጨረሻ ሰውዬው ገባው:: ያ አስፈሪና ጭጋግ የመሰለው ፊቱ ተፈታ:: የደስታ ውጋጋን ፊቱ ላይ ያበራ ጀመር:: «እውነትም ሊያሳድሩኝ ይሆን» ሲል ራሱን ጠየቀ:: ከደስታ ብዛት እንደ እብድ ይቀባጥር ጀመር::

«እውነት ነው? እንዴት? ሊያሳድሩኝ ነው? ወይስ አታሳድሩኝም? ወንጀለኛውን! ሌሎች እንዳደረጉት ሁሉ 'አንተ ውሻ፣ ከዚህ ውጣ' በማለት ፋንታ ልጄ እያሉ በአክብሮት ጠሩኝ እኮ! አሁን ከልብም ነው? ከዚህ እንዳድር ፈቅደውልኛል? ጥሩ ሰዎች ናችሁ:: እኔ ደግሞ ገንዘብ ስላለኝ በሚገባ እከፍላችኋለሁ:: ይቅርታ ብቻ፣ ድፍረት ባይሆንብኝ፣ የሆቴሉ ባለቤት እርስዎ ይመስሉኛል::» ስምዎን ልጠይቅ! የጠየቁኝን እከፍላለሁ:: ጥሩ ሰው ነዎት:: የሆቴሉ አስተዳዳሪና ባለቤት ነዎት ወይስ አይደሉም?»

«ለእዚህ ቤት የምኖር መነኩሴ ነኝ» አሉ ጳጳሱ በገርምታ::

«መነኩሴ» አለ ሰውዬው:: «እህ... ፍጹም መነኩሴ! እንግዲያውስ ገንዘብ አያስከፍሉማ? የተጎዳን የሚረዱ፣ የተጠቃን የሚያጽናኑ፣ ለነፍስዎ ያደሩ ሰው ነዎታ! አይደሉም? የዚያ ትልቅ ቤተክርስቲያን ቄስ-ገበዝ መሆንዎ ነዋ! አዎን፣ መሆን አለብዎት:: እንዴት ያለሁ ደደብ ሰው ነኝ! እንዴት ቆብዎን ልብ አላልኩም::»

ሰውዬው የጥያ የቀጡን እያለ ስልቻውንና ዱላውን ከአንድ ጥግ አስቀምጦ መታጠቂያውን ወደ ቦርሳው ከመለሰ በኋላ ቁጭ አለ::

«አባቴ፣ ሰብአዊ ርህራሄና ፍራሃ እግዚአብሔር ያደረብዎት ሰው ነዎት:: እኔን እንደሌሎች ሰዎች አላንቋሸሹኝም:: የሀዋርያት ምሳሌ ነዎት:: እንደ እርስዎም ያለ ካህን ያለ አይመስለኝም:: እንግዲያውማ ገንዘብ አይቀበሉኝም ማለት ነው?»

«የለም» አሉ ጳጳሱ፣ «ገንዘብህን ያዘው» ካሉ በኋላ በኃይል ተነፈሱ::

ሰውዬው ልፍለፋውን ቀጠለ:: «አባቴ ብፁዕ ወቅዱስ ለነፍስዎ ያደሩ ነዎታ! ከእዚያ ከነበርኩበት እስር ቤት አንዳንድ ቀን ትምህርት ይሰጡን ነበር:: አንድ ቀን አንድ ጳጳስ አየሁ:: ሰዎች አቢቱትን እያሉ ሲጠርዋቸው ሰምቼአለሁ:: ማርሴይ ከተባለ ሥፍራ የመጡ ሲሆን የዚያ አገር ሊቀ ጳጳስ እንደነበሩ ተነግሮናል:: ጳጳሱ የጳጳሳት ጳጳስ ናቸው ብለውናል:: አዬ እንዴት እንደምዘበርቅ:: እኔ እንደሆንኩ ምንንም አልያዝኩትም፣ አልገባኝም ነበር:: ይቅርታ ያድርጉልኝ:: እኛ መሐይሞች እኮ ምንም አናውቅም:: አንድ ቀን ከቤተመቅደሱ ውስጥ ሆነው ቅዳሴውን መሩ:: አንድ ሾል ያለና ከወርቅ የተሠራ ነገር ራሳቸው ላይ አጥልቀው የፀሐይ ጨረር ከላዩ ላይ ሲያርፍ



በጣም የሚያብረቀርቅ ነገር ነበር:: በሰልፍ እንደገቡም ስለተደረደሩ ብዙም ብርሃን ስላልነበረ ጳጳሱ በግልጽ አልታዩኝም:: ንግግር አድርገውልናል:: ግን በመካከላችን ርቀት ስለነበረ የሚሉትን በግልጽ ለመስማት አልቻልንም:: ጳጳስ ማለት እንግዲህ ይኸው ነው መሰለኝ::»

እንግዳው ሲናገር ጳጳሱ የተበረገደውን በር ዘጉ:: መዳም ማግሎዋር ተጨማሪ አንድ ሳህን ይዘው መጥተው ከጠረጴዛ ላይ አኖሩ::

«መዳም ማግሎዋር» አሉ ጳጳሱ፣ «አሁን ያመጡትን ሳህን እሳቱ ከሚነድበት ቀረብ አድርገው ቢያኖሩት::» ከዚያም ወደ እንግዳው ዞር ብለው «የውጩ አየር በጣም ይቀዘቅዛል፣ ሳይበርድህ አልቀረም ልጄ» አሉት::

ጳጳሱ ረጋ ባለ መንፈስና በሚጋባ ድምፅ «ልጄ» ብለው በጠሩት ቁጥር የሰውዬው ፊት ፈገግ ይላል:: የተፈረደበት ወንጀለኛን 'ልጄ' ብሎ መጥራት ማለት ባህር ላይ ቁጭ ብሎ በውሃ ጥም ለሞት ለተቃረበ ሰው አንድ ብርጭቆ ንጹህ ውሃ እንደመስጠት ያህል ነበር:: ሰው የናቀው ክብር ይጠማዋል::

«ፋኖሱ በቂ ብርሃን የለውም» አሉ ጳጳሱ::

መዳም ማግሎዋር ገባቸው:: ወደ ጳጳሱ መኝታ ቤት ሄደው ሁለት ከብር የተሠሩ ረጃጅም የሻማ ማብሪያ አመጡ:: ሻማ ለኩሰው ከሻማ ማብሪያው ላይ ካደረጉ በኋላ ከጠረጴዛው ላይ አስቀመጥዋቸው::

«አባቴ» አለ ሰውዬው፣ «ጥሩ ሰው ነዎት፤ እኔን አይንቁኝም፣ አያንቋሸሹኝም:: ከቤትዎ ከማስጠጋት አልፈው በትህትና ያናግሩኛል:: ለእኔ ክብር ብለው ተጨማሪ ሻማ እንዲበራ አዘዙ:: እኔም የሕይወት ታሪኬን ሳልደብቅ ከየት እንደመጣሁና ምን ያህል የተሰቃየሁ መሆኔን ገልፀኩልዎት::»

ከአጠገቡ ተቀምጠው የነበሩት ሰው ቀስ ብለው እጁን ይዘው የሚከተለውን ተናገሩ::

«ማን እንደሆንክ እንድትነግረኝ አያስፈልግም:: ይህ የእኔ ቤት አይደለም፣ የክርስቶስ ቤት ነው:: እርሱ ማንኛውንም ባይተዋር ችግር፣ መከራና ስቃይ እንዳለበት እንጂ ማን እንደሆነ አይጠይቅም:: አንተ መከራን ቀምሰሃል፣ ተርበሃል፣ ተጠምተሃል:: ስለዚህ ቤቴ ቤትህ ነው:: ለዚህም እንድታመሰግነኝ አልፈልግም:: አስጠጋኸኝም ብለህ አትጠይቀኝ:: ይህ ቤት ማረፊያ ለሚፈልግ፣ ለተቸገረ እንጂ የማንም ቤት አይደለም:: ማነው መንገደኛው? ማነው እንግዳ? እመነኝና አንተ ከእኔ ይበልጥ ቤተኛ ነህ::

ከእዚህ ቤት ያለው ነገር ሁሉ ያንተ ነው፡፡ ያንተን ስም ማወቅ ለምን ያስፈልገኛል? ከዚህም በላይ አንተ ሳትነግረኝ እኔ አውቄዋለሁ፡፡»

ሰውዬው በመገረም አፉን ከፈተ፡፡

«እርግጥ ነው?፡፡ ማን እንደሆንኩ አውቀዋል?»

«አዎን» አሉ ጳጳሱ፤ «ስምህ ወንድሜ ነው፡፡»

«ቢቃ... ቢቃ አባቴ» ሲል ሰውዬው ጮኸ፡፡ «ከዚህ ቤት ስገባ ጠኔ ይዞኝ ነበር፡፡ ግን የደግነትዎ ብዛት ይሁን እኔ እንጃ፤ ምን እንደነካኝ አላውቅም፤ ምንም ሳልበላ ያ ሁሉ ረሃብ ተወግዶልኛል፡፡»

ጳጳሱ እንደገና አትኩረው ከተመለከቱት በኋላ «ብዙ መከራና ስቃይ ደርሶብሃል» አሉት፡፡

«አወይ! ያቺ ቀይዋ ጥብቆ፤ የብረቱ ሰንሰለት፤ የእንጨቱ መኝታ፤ ሙቀቱ፤ ብርዱ፤ ግርፋቱ፤ ከዚያ የነበሩ ባሮች... ኧረ ምን ቅጡ፤ አንድ ቃል ቢተነፍሱ የጨለማ ቤቱ፤ በታመሙ ጊዜ እንኳን ከዚያ ጨለማ ቤት በብረት ሰንሰለት ተጠፍሮ መኖሩ! ውሾች፤ ውሾች እንኳን ከዚያ የተሻለ ኑሮ ነው የሚኖሩት፡፡ አሥራ ዘጠኝ ዓመት! አርባ ስድስት ዓመቴ ነው፡፡ አሁን ደግሞ መታወቂያዬ የወንጀለኛ ነው፡፡ ይኸው ነው ታሪኬ፡፡»

«ይሁን» አሉ ጳጳሱ፤ «የስቃይና የመከራን ቤት ለቅቀህ መጥተሃል፡፡ አሁን ግን ስማኝ ያንን አስፈሪና አሳዛኝ ቦታ በሰዎች ላይ ጥላቻንና ቂምን አሳድሮብህ የምትለቅቀው ከሆነ የሚታዘንልህ ሰው ነህ፡፡ በበጎ ፈቃድ፤ በጨዋነትና በሰላም የምትለቀው ከሆነ ግን ከሁላችንም ትበልጣለህ፡፡»

በዚህ ጊዜ መዳም ማግልዋር ገበታ መቅረቡን ያበስራሉ፡፡ ከቀረበው ገበታ ሾርባ፤ ሥጋ፤ አይብና ዳቦ ይገኛል፡፡ የሚጠጣ ቪኖም ነበር፡፡

ጳጳሱ የደስታ፤ የእርካታ ስሜትና «እንኳን ደህና መጣህ» የሚል ፈገግታ እየታየባቸው «እራት ቀርቦአል» አሉ ወደ እንግዳው እየተመለከቱ፡፡ እንግዳውን ከቀኛቸው አስቀመጡት፡፡ መድምዋዜል ባፕቲስታን ከበስተግራቸው ተቀመጡ፡፡ ጳጳሱ ማዕዱን ከባረኩ በኋላ ከሾርባው ለራሳቸው አወጡ፡፡ ሰውዬው ምግቡ ላይ ተረባረበ፡፡

«ገበታው ላይ አንድ ነገር የጎደለ መሰለኝ» አሉ ጳጳሱ በድንገት፡፡

መዳም ማግልዋር ገበታ ሲያቀርቡ ያዘጋጁት ለጊዜው አስፈላጊ የነበሩትን ሦስት ከብር የተሠሩ ሣህኖችን ብቻ ነበር፡፡ በዚያ ቤት ባህል እንግዳ በመጣ ቁጥር ስድስቱንም ከብር የተሠሩ ሣህኖች ከገበታው ላይ መደርደር ነበረባቸው፡፡ ለትራፊ ሳይሆን ሌላም እንግዳ ቢመጣ ደስ ይለናል



በማለት ቸርነታቸውን ለማሳየት ነው፡፡

መዳም ማግልዋር የጳጳሱ አስተያየት ስለገባቸው ወዲያው ከመቅጽበት የተቀሩት የብር ሣህኖች መጥተው ከእያንዳንዳቸው ትይዩ ተቀመጡ፡፡

ከእራት በኋላ ጳጳሱ እህታቸውን ተሰናብተውና አንድ ሻማ ለራሳቸው፤ አንድ ሌላ ደግሞ ለእንግዳው ለመስጠት ሁለት ሻማ ይዘው ተነሱ፡፡ ከዚያም «ልጄ ክፍልህን ላሳይህ» አሉት፡፡ ሰውዬው ተከተላቸው፡፡

ለእንግዳው የተዘጋጀው ክፍል በጳጳሱ መኝታ ቤት አልፎ ነበር የሚገኘው፡፡ እንግዳው ልክ ከጳጳሱ መኝታ ቤት ሲያልፍ መዳም ማግልዋር እነዚያ የሚያማምሩ የብር ሣህኖች ከብፁዕነታቸው መኝታ ቤት ውስጥ ይገኝ ከነበረው ቡፌ ውስጥ እያስቀመጡ ስለነበር ዣን ቫልዣ ተመለከተ፡፡ ዘወትር ማታ ማታ መዳም ማግልዋር ከመተኛታቸው በፊት ሣህኖቹን አጣጥበው ከቡፌው ውስጥ ነው የሚያስቀምጧቸው፡፡

የእንግዳው አልጋ ከነበረበት ክፍል ደረሱ፡፡ ሰው ያልተኛበት ንጹህ ነጭ አንሶላ ነው የተነጠፈው፡፡ ሰውዬው ሻማውን አስተካክሎ ከአንዲት አነስተኛ ጠረጴዛ ላይ አስቀመጠ፡፡

«መልካም እንቅልፍ፤ ነገ ጠዋት ከመሄድህ በፊት ላሞች ስላሉን ትኩስ ወተት ጠጥተህ ትሄዳለህ» አሉ ጳጳሱ፡፡

«አመሰግናለሁ አባታችን» አለ እንግዳው፡፡»

የምስጋና ቃሉን እንደደረደረ ወዲያው ከመቅጽበት እነዚያ ሁለት ሴቶች ከዚያ ቢኖሩ ውሃ ሊያደርጋቸው ይችል የነበረ ነገር ይናገራል፡፡ ወደ ጳጳሱ ዞር ብሎና ፊቱን ለዋውጦ በሻከረ ድምፅ ጮክ እያለ «አሁን ጥሩ ነው፤ ከመኝታ ቤትዎ አጠገብ ነው ያስተኙኝ፡፡ ለመሆኑ በጉዳዩ አስበውበታል? ነፍሰ-ገዳይ አለመሆኔን ማን ነግሮት?» ሲል ጠየቃቸው፡፡»

«እግዚአብሔር ያውቃል» ሲሉ በእርጋታ መለሱለት፡፡

ከዚያም ምንም ሳይጨነቁና ድምፅ ሳያሰሙ ከራሱ ጋር እንደሚነጋገር ወይም በጥሞና ጸሎት እንደሚያደርስ ሰው ከንፈራቸውን ካንቀሳቀሱ ሰውዬውን ከባረኩ በኋላ በቀጥታ ወደ ክፍላቸው ሄዱ፡፡

ከጥቂት ጊዜ በኋላ ከዚያ ቤት የነበረ ሰው ሁሉ እንቅልፍ ወሰደው፡፡

እኩለ ሌሊት ላይ ዣን ቫልዣ ነቃ፡፡

ዣን ቫልዣ ገበሬ ሲሆን የተወለደው ብሪ በምትባል ከታወቀ ድሃ ቤተሰብ ነው፡፡ በልጅነቱ ትምህርት ቤት ገብቶ የመማር እድል ባለማግኘቱ መሃይም ነው፡፡ ከአደገ በኋላ ከተማ ውስጥ በአትክልተኛነት ሥራ ጀመረ፡፡

ዣን ቫልዣ በተፈጥሮው ለሰው አሳቢ እንጂ አዛኝ አልነበረም:: ቤተሰቦቹ በልጅነቱ ነው የሞቱት:: እናቱ የሞቱት ታምመው ሲሆን አባቱ ከዛፍ ላይ ወድቀው ነው:: አባቱም እንደ እርሱ አትክልተኛ ስለነበሩ ዛፍ ሲመከርክሙ ከትልቅ ዛፍ ላይ ወጥተው ሳለ በድንገት ወድቀው ነው ሕይወታቸው ያለፈው:: ከቤተሰቡ መካከል በሕይወት የቀረች ከእርሱ ሌላ አንዲት እህት ነበረችው:: የእህቱ ባል ሰባት ልጆች ጥሎላት ይጠፋል:: ዣን ቫልዣን ያስጠጋችው እህቱ ስትሆን ባልዋ እስከጠፋ ድረስ ተንከባክባ ነበር ያሳደገችው:: ባልዬው ሲሞት የትልቁ ልጃቸው እድሜ ስምንት ዓመት ሲሆን የመጨረሻው ልጅ እድሜ አንድ ዐመት ነበር:: ዣን ቫልዣ በዚያን ጊዜ 25 ዓመቱ ነበር:: እርሱ በተራው የልጆቹን አባት ተክቶ እህቱንና ልጆችዋን ይረዳ ጀመር:: የወጣትነት ዘመኑን አዳጋችና አድካሚ ግን ብዙ ገቢ በማያስገኝ ሥራ ላይ ነበር ያሳለፈው:: በጊዜ ማጣትና ድኅነት ምክንያት በእፍላ ዘመኑ የከንፈር ወዳጅ እንኳን አልነበረውም:: እንዲያውም ከነአካቴው ለፍቅር ጊዜ አልነበረውም ማለት ይቻላል::

ማታ ማታ ከመሸ በኋላ ከቤቱ ተመልሶ ቃል ሳይናገር ያገኘውን ይበላል:: አንዳንድ ቀን ያቺን የምስኪን እራቱን ሲበላ እህቱ ከቀረበለት ምግብ ጥቂቱን እንደገና እየወሰደች ለልጆችዋ ትሰጥበታለች:: ይህ ሲሆን በረጅም ፀጉሩ ፊቱን ሸፍኖ በዝምታ የተረፈችውን ይበላል:: ምንም ነገር እንዳልሆነ በመቁጠር ራሱን ለማታለል ይሞክራል:: ምርጫም አልነበረውም::

ዛፍ በሚገረዝበት ወራት በቀን እስከ 18 ሱስ ያገኛል:: ሥራ ሳይመርጥ ያገኘውን ይሠራል:: እህቱም ትሠራለች:: ቢሆንም ራሳቸውን ያልቻሉ ሰባት ልጆችን ማሳደግ ቀላል አልነበረም:: ገንዘቡ ስላልበቃቸው ቤተሰቡ ችግር ቀስ በቀስ እያለ የሚያሳድደው አሳዛኝ ቤተሰብ ሆነ:: የአንድ ዘመን ክረምት በጣም የከፋ ነበር:: በዚህ ጊዜ ዣን ቫልዣ ሥራ አልነበረውም:: በዚህ የተነሣ ቤተሰቡ የሚልስ ወይም የሚቀመስ ነገር ያጣል::

አንድ ቀን እሑድ ማታ የአንድ ዳቦ መጋገሪያ ቤት ባለቤት ሊተኛ ሲል የዳቦ ቤቱ መስታወት ሲሰበር ይሰማል:: የሰውዬው መኖሪያ ቅጥር ግቢው ውስጥ ስለነበር በጊዜ በመድረሱ በተሰበረው መስታወት በኩል አንድ ሰው እጁን አሾልኮ ዳቦ ሲሰርቅ ያየዋል:: ሌባው ዳቦውን ይዞ ሮጠ:: የዳቦ ቤቱ መስታወት የሰበረው በቡጢ ስለነበር እጁ ይደማል:: ስለዚህ ዳቦው የተወሰደው በሌባ ስለመሆኑ ሌላ ማስረጃ አላስፈለገም:: ሌባው ሰውዬ ዣን ቫልዣ ነበር::

ይህ የሆነው በ1795 ዓ.ም መጨረሻ ነው:: ዣን ቫልዣ የተዘጋ ቤት ጨለማን ተገን በማድረግ ሰብሮ ለመስረቅ በመሞከሩ «ወንጀለኛ ነው» ተብሎ ተፈረደበት:: ብያኔው ለአምስት ዓመታት በባርነት የመርከብ ቀዛፊ



ሆኖ እንዲሠራ ነበር::

ዣን ቫልዣ አንገቱ በብረት ሰንሰለት ታስሮ ቱሉን ወደተባለ እስር ቤት ተወሰደ:: ጉዞው ሃያ ሰባት ቀን ወሰደበት:: የተጓዘው በእንስሳ በሚጎተት ጋሪ ነበር:: ከተወሰነለት ሥፍራ እንደደረሰ ጥብቆ አለበሱት:: ያለፈው ታሪኩ! ስሙ እንኳን ሳይቀር ተለወጠ:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ስሙ ዣን ቫልዣ ሳይሆን ቁጥር 24 ሺህ 601 ሆነ::

ከዚያ በኋላ እህቱ ምን ሆነች? ሰባት ልጆችዋስ ምን ደረሱ? ስለዚህ ጉዳይ ራሱን ያስጨነቀ አልነበረም:: ጥቂት የዛፍ ቅርንጫፎች ከትልቅ ዛፍ ግንድ ሲቆረጥ ማነው ስለቅርንጫፎቹ የሚጨነቀው?

አራተኛ ዓመቱን ሲያገባድድ ዣን ቫልዣ ከእስር ቤት አምልጦ ነፃነቱን የማግኘት እድል አጋጠመው:: ከእንደዚያ ባለ አስፈሪ ቦታ ያሉ ሰዎች ዘወትር እንደሚተባበሩ ሁሉ የእርሱም የሥራ ጓደኞች ረድተውት አመለጠ:: ለሁለት ቀናት በየጥሻውና በእርሻ ቦታ እየተሸሎከሎከ ቆየ:: በሁለተኛው ቀን ግን ወደማታ እንደገና ተያዘ:: ለ36 ሰዓት ያህል እህል አልቀመሰም:: እንቅልፍም አልተኛም:: ለማምለጥ በመሞከሩ የእሥራት ዘመኑን በሦስት ዓመት ፍርድ ቤቱ አራዘመበት:: በጠቅላላው ስምንት ዓመት ሆነበት ማለት ነው:: በስድስተኛው ዓመት እንደገና ለማምለጥ ሞክሮ ሳይሳካለት ቀረ:: ማታ ስም ሲጠራ 'አቤት' ሳይል በመቅረቱ ጥሩምባ ተነፋ:: ማታውኑ በአካባቢው የነበሩ ሰዎች ከመርከብ ስር ተሸሽጎ አገኙት:: ዘበኛው ሊይዘው ሲል ተናነቀው:: ወንጀሉ እጥፍ ሆነ:: ለማምለጥ በመሞከሩና ዘበኛ በመተናነቁ ለዚህ ጥፋቱ አምስት ዓመት ተፈረደበት:: አሥራ ሦስት ዓመት ሆነ:: በአሥረኛው ዓመት እንደገና ለማምለጥ ሞክሮ አሁንም ሳይሳካለት ቀረ:: ለዚህም ሙከራው ሦስት ዓመት ተፈረደበት:: አሥራ ስድስት ዓመት! በመጨረሻም በአሥራ ሦስተኛ ዓመቱ ይመስለኛል እንደገና ለማምለጥ ሙከራ አድርጎ ከአራት ሰዓት በኋላ እንደገና ተያዘ:: ለአራት ሰዓት ከእስር ቤት በመጥፋቱ አሁንም አራት ዐመት ተፈረደበት:: ሃያ ዓመት! ዳቦ በመስረቁ ከእስር ቤት የገባው በ1796 ዓ.ም ሲሆን ከአሥራ ዘጠኝ ዓመት እሥራት በኋላ ግን ለማምለጥ ቻለ::

መርከብ ቀዛፊዎች ከሚታሰሩበት ሲገባ እየተንቀጠቀጠና እያለቀሰ ነበር:: ያን ሥፍራ ሲለቅ ግን ልቡ ደንድኖ ነበር የወጣው:: ከዚያ ሲገባ ተስፋ ቆርጦ ነበር የገባው! ሲወጣ ግን ተስፋ ቢስ ብቻ ሳይሆን ጨካኝም ሆኖ ነው የወጣው::

ታዲያ የዚህ ነፍስ ሕይወት ምን ይሆን!

ታሪኩን ለማውሳት እንሞክር እስቲ:: የሰውዬው ችግር በሕብረተሰቡ

የተፈጠረ ስለሆነ ይኸው ሕብረተሰብ እነዚህን ነገሮች አጢኖ መመልከት ይኖርበታል።

## ፫

ቀደም ሲል እንዳልነው ዣን ቫልዣ አላዋቂ ነው። ግን ደደብ አይደለም። በተፈጥሮው ጭምት ነው። ሰንኳላው እድሉ ደግሞ በይበልጥ እንዲጨምትና እንዲያስተውል ገፋፍቶታል። ሲገፍ፣ በሰንሰለት ሲጠፈር፣ ጨለማ ቤት ሲታሰር፣ ሰውነቱ በድካም ብዛት ዝሏል። የሌሊት ቁር ሲያቆራምደው፣ የቀን ፀሐይ ሲያወራጨው፣ እንዲሁም ከእንጨት ላይ ተኝቶ ዘወትር ከአሳብ ውስጥ እየዋኘ ከኅሊናው ጋር ሲሟገት የኖረ ሰው ነው።

ራሱን እንደ ፍርድ ቤት ስለቆጠረ ምርመራውን በመጀመሪያ ከራሱ ይጀምራል። ያለ አግባብ የተቀጣ የዋህና ቀና ሰው አለመሆኑን ኅሊናው ያውቃል። ሕገ ወጥ ተግባር መፈጸሙን አይክድም። ምናልባት ያንን አንድ ዳቦ ቢለምን ኖሮ አይነፈግም ነበር ይሆናል። አዛኝ ወይም አሠሪ እስኪያገኝ ድረስ ደግሞ መታገስ ነበረበት። ለእነዚያ የትም በትኖአቸው ለቀረው ምስኪኖችም ይኸው ይበጅ ነበር። ስለዚህ የፈጸመው ተግባር የሞኝ ነው ለማለት ይቻላል። አንድ አርቆ ለማየት የማይችል ድሃ ዓለምን በጉልበት አሸንፋለሁ ብሎ ቢጋፈጥ ወይም ችግሮችን በሌብነት እወጣለሁ ብሎ ቢታሰል ስህተተኛነቱን ግሃድ ያወጣል።

ነገር ግን በአሳዛኝ ታሪኩ ውስጥ ስህተት የፈጸመው ዣን ቫልዣ ብቻ ነው? እንደ እርሱ ያለ ትጉህ ሠራተኛ ሥራ አጥቶ መንከራተቱና ዳቦ ማጣቱ የሚያሳዝን አይደለም? ስህተት ፈጽሞ ጥፋተኛነቱን ቢያምንም ቅጣቱ ግን ቅጥ ያጣና የአውሬዎች ብያኔ መሆኑ አግባብ ነው? ወንጀለኛ ወንጀል ለመሥራት ካለው ፍላጎት ይበልጥ ሕግን አንተርሶ ቅጣትን የማክረር ባህርይ ትክክል ነው? የቅጣት ክብደት ወንጀልን ለማጥፋትና በውጤቱ ሁኔታዎችን ለማሻሻል ሳይሆን የተበዳዮችን ስህተት ለማጉላትና በቸልተኞች ስህተት ለመቀየር፣ ወንጀለኞችን ከሚገባው በላይ ለማሰቃየት፣ አበዳሪን በባለዕዳ ለመለወጥ ከሆነ ይህ ተገቢ ነው?

ዣን ቫልዣ ይህን እያሰላሰለ «እውነቱ ቢወጣ ማነው ጥፋተኛ?» ሲል ራሱን ይጠይቃል።

ሕብረተሰቡ አንድ ጊዜ በምክንያት ባልተደገፈ ግድየለሽነት፣ በለ



ጊዜ ደግሞ ርህራሄ በተለየው ዓይን እያየ በአባሉቹ ላይ ተመሳሳይ ፍርድ የመበየን ኃይል ቢኖረውም ሕብረተሰቡ ውስጥ እድል በሚያፈራው ሀብት እጅግ ዝቅተኛ የሆነ ድርሻ የሚደርሳቸው ምስኪኖችን እጅግ አድርጎ ማሳደድ የጭካኔ አይደለም?

ዣን ቫልዣ እነዚህንና ሌሎችንም ጥያቄዎች እየጠየቀ በሕብረተሰቡ ላይ ፈርዶ ብያኔ ይሰጣል። ብያኔው በሕብረተሰቡ ላይ የከረረ ጥላቻን ማሳደር ነበር። በሕይወት ዘመኑ የደረሰበት ፈተናና ስቃይ የሕብረተሰቡ ውጤት መሆኑን አመነ። ምናልባት አንድ ቀን እድል ቢገጥመው ሕብረተሰቡን እንደሚበቀል ለራሱ ቃል ይገባል።

የሕብረተሰቡ አባሎች ሕይወቱን አበላሹበት። ከቁጡ ፊታቸው ሌላ ያሳዩት ነገር አልነበረም። ማንም ቢሆን ለመሳላጥ ካልሆነ በስተቀር ፍቅርን አላሳየውም። ከሕፃንነቱ ማለት ከእናቱና ከእህቱ ከተለየ ጀምሮ ማንም ቢሆን ርህራሄ በተለየው በክፉ ቃል እንጂ በጥሞናና በሰላም ያነጋገረው የለም። በስቃይ ላይ ስቃይ እየታከለበት በሄደ ቁጥር ሕይወት ጦርነት መሆኑን አመነ። በጦርነቱም እርሱ ድል እንደተመታ አወቀ። ከጥላቻ በስተቀር ሌላ የተማረው ነገር አልነበረም። እስር ቤት እያለ ይህን ትምህርቱን ለማጠናከርና ከዚያም ሲወጣ ይዞት እንደሚወጣ ወሰነ። ዣን ቫልዣ በዚህ ሳይቆም ለስቃዩ ምክንያት የሆነውን ሕብረተሰብ ለፍርድ አቅርቦ በእርሱ ላይ ብያኔ መስጠት ብቻ ሳይሆን ሕብረተሰቡን የፈጠረውንም አምላክ ጭምር አወገዘ።

ዣን ቫልዣ ከታሠረበት ቱሉን ከተባለ ቦታ እንደ እርሱ ያሉ ምስኪኖች የሚማሩበት ትምህርት ቤት ራሳቸውን ለሌሎች መስዋዕት በሚያደርጉት ጥቂት ግለሰቦች ተከፍቶ ነበር። አንዳንድ ጊዜ ትምህርትና ንቃት ለተንኮልና ለክፋት በር የሚከፍቱ ቢሆንም በአርባ ዓመቱ ትምህርት ቤት ገብቶ መጻፍና ማንበብ ተማረ።

እነዚያ 19 የስቃይና የባርነት ዘመን ይህ ነፍስ በአንድ ጊዜ እየሞተና በሌላ ጊዜ ሕይወት እየዘራ ነው የኖረው። የሕይወቱ ግድግዳ በአንድ በኩል ብርሃን ሲገባው በሌላ በኩል ጨለማ ቦርቡሮታል።

ዣን ቫልዣ በተፈጥሮው ክፉ ሰው አልነበረም። ከእስር ቤቱ ሲደርስ ልቡ ቀና ነገር ነበር የሚያስበው። እዚያ ውስጥ እያለ ግን ሕብረተሰብን ጠልቶ እርሱም ክፉ ሰው እንደሆነ አመነ።

አንድ መዘንጋት የሌለብን ነገር አለ። ይኸውም ዣን ቫልዣ እስር ቤት ውስጥ ከነበሩት ሰዎች ሁሉ በአካል ጥንካሬና ጉልበት እጅግ የላቀ እንደነበር ነው። ከባድ ሥራ በመሥራት፣ ወንከሬ ሽቦ በመጠምዘዝ፣

ክብደት ያለውን ነገር በማንሳት የአራት ሰዎች ጉልበት አይስተካከለውም።

አንድ ጊዜ የቤት ጥገና ሥራ እየተካሄደ ሳለ ተንጠልጣይ ግምብ ደግፎ ይዞ የነበረው ብረት ሾልኮ ግንቡ ሊፈርስ ሲል በአጋጣሚ እዚያ የነበረው ዣን ቫልዣ ሰዎች እስኪደርሱለት ድረስ ብቻውን ግንቡን ደግፎ እንዳቆመ ይነገራል።

ቅልጥፍውና የሰውነቱ መታዘዝ ጉልበቱን የሚያስንቅ ነበር። የወንጀለኞች የዘወትር ሕልም የማምለጥ እቅድ ማውጣት ሲሆን ይህም አንዳንድ ጊዜ ጉልበት ከትሎታ ጋር ይሰጣቸዋል። በአእዋፍና በዝንቦች ዘወትር እንደቀኑ የሚኖሩት እስረኞች እንደ እነርሱ መብረር ይፈልጋሉ። ዣን ቫልዣ የዚህ ዓይነት ትናት ስላደረበት የማይሞክረው ነገር አልነበረም። ከማዕዘንና ከቋጥኝ ላይ እየዳሁ መውጣት፣ በጀርባ መንሸራተት፣ ከረጅም ከፍታ መዝለልና የመሳሰሉትን መፈጸም ለዣን ቫልዣ የእለት ተእለት ተግባር ነበር። አንዳንድ ጊዜ እርሱ የሚሠራቸው ነገሮች ታምራዊ እንጂ ማንም ሰው የሚሠራው አይመስልም ነበር። አንዳንድ ቀን እንዴት እንደወጣ ሳይታወቅ ከፎቅ ቤት ጣራ ላይ ወጥቶ ይገኛል።

ብዙ አይናገርም። ሁልጊዜም እንደተከሳተረ ነው። ጥርሱን አሳይቶ አያውቅም። የእስረኞች የጭንቀት ድምፅ ስሜቱን ይነካው እንደሆን እንጂ ሌላ ነገር ስሜት አይሰጠውም። ለተመለከተውና ላጤነው ዘወትር ሳያቋርጥ በአስፈሪ የአሳብ ባህር የተዋጠ ለመሆኑ ከፊቱ ላይ ይነበባል።

ብቅ ጥልቅ በሚልና ባልተሟላ ሕይወት ታፍኖ በተያዘ እውቀት አማካይነት በጭላንጭል ለማየት እንደሚሞክር ነፍሱ-አድን አስፈሪ የሆነ ግዙፍ አካል እንደተጫነው ይሰማዋል። ከዚያ ይቅርታቢስና አስፈሪ ከሆነው፣ ከተጫነው ነገር ለማምለጥ አንገቱን ቀና አድርጎ ዓይኖቹን ለመግለጥ ሲሞክር ሥልጣኔ ብለን የምንጠራው ነገር ያስገኛቸው ነገሮች፣ ሕጎች፣ የሰዎች አስከፊ ገጽታዎችና ሥራቸው ተከማችተውና ከቁጣና ከፍርሃት ጋር ተደባልቀው በአሳብ ያያቸዋል። ቀስ በቀስ ግን ከእርሱ እየራቁ ወደላይ አሻቅበው ወጥተው ከፊቱ ሲሰወሩ ይመለከታል።

ዣን ቫልዣ በዚህ ዓይነት ተጨባጭ ዓለም አስፈሪ በሆነ መናፍስት ተሞልቶ፣ አስፈሪው የመናፍስት ዓለም ደግሞ በእውን ነገር ተተክቶ በቃላት ሊገለጽ በማይችል ሁኔታ በአካሉ ውስጥ እየተቀረጸበት የኖረ ሰው ነው።

አንዳንድ ጊዜ እስር ቤት ውስጥ ሆኖ ድንገት ሥራውን አቁሞ ማሰብ ይጀምራል። ቀደም ሲል የነበረው፣ አሁን ግን የዋገተው የማመዛዘን ችሎታው ጨርሶ እየጠፋ በእርሱ ላይ የደረሰው ሁሉ ከሥርዓት ውጪ፣



በአካባቢው የሚያየው ነገር ሁሉ ያልሆነና የማይሆን ይመስለዋል። «ይህ ሁሉ ሕልም ነው» እያለ እርስ በራሱ ይነጋገራል። ከእርሱ ጥቂት ርቆ የቆመውን የእስር ቤት ኃላፊን አተኩሮ ይመለከታል። ኃላፊው አንድ ዓይነት መንፈስ እንጂ ሰው ሆኖ አይታየውም። ሆኖም ይህ መንፈስ በድንገት በዱላ ይጠልዘዋል።

ለእርሱ የምናየው ዓለም እውንነት አጠራጣሪ ነው። እንዲያውም ከእነካቴው ለዣን ቫልዣ «ፀሐይ የለችም፣ ክረምትና በጋ አይፈራረቁም፣ ጠፈር የሚባል ነገር የለም» ቢባል ከእውነት የራቀ አይሆንም። ለእርሱ የአካሉ መጀመሪያና መጨረሻ የሰው ልጆች ያወጡት ሕግና የሰውን ዘር በአጠቃላይ መጥላት ሲሆን የዚህም ውጤት ማን፣ ምን ሳይባል በሕይወት ያለን ማንኛውንም ፍጡር የማጥፋት ምኞት ነው። የዚህ ዓይነቱ ጥላቻ በተወሰነ ወቅት በመለኮት ኃይል ካልተገታ በስተቀር አደገኛ ነው። ስለዚህ ዣን ቫልዣን «እጅግ አደገኛ ሰው» ብሎ መናገሩ ስህተት አልነበረም።

ከዓመት ዓመት ይህ ሰው ቀስ በቀስ እያለ በይበልጥ በአደገኛ ሁኔታ እየደነደነና እየጨከነ ሄደ። ይህም ደንዳና ፍጡር የደረቀ ዓይን ነበረው። ለአሥራ ዘጠኝ ዓመት እስር ቤት ውስጥ ሲቀመጥ አንድ ቀን እንኳን እንባ አልወጣውም።

## ፬

ከቤተክርስቲያን አናት ላይ የተሰቀለው ሰዓት ስምንት ሰዓት ሲደውል ዣን ቫልዣ ከእንቅልፉ እንደገና ነቃ። ከአራት ሰዓት በላይ ጥሩ እንቅልፍ ወስዶት ተኝቷል። ድካሙ ሁሉ ወጣለት። ለዚህን ያህል ጊዜ የእረፍት ሰዓት አግኝቶ አያውቅም። ዓይኑን ገልጦ በአካባቢው በሰፈነው ጨለማ ዘልቆ ለማየት ሞከረ። ለማየት ባለመቻሉ እንደገና እንቅልፍ እንዲወስደው ዓይኖቹን ጨፈነ።

ቀኑን ሙሉ አእምሮ በብዙ ነገሮች ተበጥብጦ ከዋለና የተለያዩ ነገሮች ከተመላለሱበት አንድ ጊዜ እንጂ ሁለት ጊዜ እንቅልፍ ሊወስድ እንደማይችል ሁሉ ዣን ቫልዣንም ሊወስደው አልቻለም። እንቅልፍ መጀመሪያ ሲመጣ ያዳፋል። ሁለተኛ ግን ቢለማመጡትም በዓይን አይዞርም። እንደገና እንቅልፍ ሊወስደው ስላልቻለ ማሰብ ጀመረ።

ብዙ ዓይነት አሳብ ከጎሊናው ውስጥ ገባ:: ግን ሴሎቹን ሁሉ እየሞጠ እርሱ ብቻ እየተመላለሰ ያስቸገረው አንድ አሳብ ነበር:: እንዚያ መዳም ማግልዋር ከጠረጴዛው ላይ የደረደሩዋቸው የሚያማምሩ ስድስት ከዛር የተሠሩ ሣህኖችና ትልቅ የብር ጭልፋ በዓይኑ ዞሩ:: በጣም ወዷቸዋል:: እጠገቡ ከጳጳሱ ትራስጌ በኩል ቡፌ ውስጥ ሲትዬዋ ሲያስቀምጧቸው አይቶአል:: ከብር የተሠሩ ጥንታዊ ቅርስ በመሆናቸው ከነጭልፋው እስከ 200 ፍራንክ እንደሚያወጡ ያውቃል::

በአሳብ እየሞተተቱ ጎሊናው ከወዲያ ወዲህ እየዋለለ አንድ ሰዓት አለፈ:: ምን ያህል ረጅም እንደሆን አንድ ሰዓት ማሳለፍ፤ ያውም ሌሊት በጨለማ፤ የቤተክርስቲያኑ ሰዓት ደወል ዘጠኝ ሰዓት መሆኑን የደረሰበት ያውቀዋል:: ስልቻውን በእጁ አበሰረ:: ዓይኑን በድንገት ገልጦ ከአልጋው ዘሎ ወረደ:: ሳያውቀው ብዙ እየዳሰሰ ፈለገና እንደያዘው ከአልጋው ጠርዝ ቁጭ አለ:: ሳያውቀው ብዙ ቀቀመጠ:: ሰዓቱ በየአሥራ አምስት ደቂቃና ግማሽ ሰዓት ደወል እየደወለ ባይቀሰቅሰውማ እስኪነጋ ድረስ በተቀመጠ:: ደወሉ «አይዞህ፣ በርታ» የሚለው መሰለው::

ተነስቶ ቆመ፤ ለመራመድ ግን አመነታ:: አንድ እርምጃ ወደፊት ተራምዶ አዳመጠ:: ሁሉም ነገር ጸጥ ብሎአል:: ቀስ ብሎ በጥንቃቄ ወደ መስኮቱ ተጠጋ:: ሌሊቱ ጥቅጥቅ ባለ ጨለማ የተዋጠ አልነበረም:: ጨረቃ በሩቁ ትታያለች:: ሆኖም ደመና ዘርግቷታል:: ደመና ጨረቃዋን በጋረዳት ቁጥር ቤቱ ትንሽ ጨለም ይላል:: ውጪው በደምብ ሲታይ እቤት ውስጥ ግን ያንገዳግዳል:: መስኮቱ አጠገብ ደርሶ መስኮቱን ሲመለከት በቀላሉ እንደሚከፈት ስለተገነዘበ ከፈተው:: ሆኖም ኃይለኛ ብርድ ስለገባ መልሶ ዘጋው:: መስኮቱ መስታወት ስለነበር እንደተዘጋ ግቢውን ቃኘ:: ግቢው በአነስተኛ ግምብ መከለሉን ተመለከተ:: ከግምቡ ውጭ ረጃጅም ዛፎች ነበሩ:: በሁለት ዛፎች መካከል ያለውን ርቀት ሲያጤን ርቀታቸው ተመሳሳይ ሆኖ ስላየው ምናልባት ማዘጋጃ ቤቱ የተከላቸው ዛፎች መሆናቸውን በመገመት ከአጥሩ ውጭ ያለው መንገድ አውራ ጎዳና መሆን አለበት ብሎ ደመደመ::

ወደ ውሳኔ አሳብ እንደደረሰ ሰው በቆራጥነት ወደ አልጋው ተመለሰ:: አቆማዳውን አንስቶ ከፈተውና ከውስጡ ምናምን ፈለገ:: አንድ ነገር አውጥቶ አልጋው ላይ አስቀመጠ:: ጫማውን ኪሱ ውስጥ ከተተ:: አልጋው ላይ ካስቀመጠው እቃ ሌላ የተቀሩትን አሳስሮ ትከሻው ላይ አኖረ:: ቆቡን አጠለቀና ዱላውን ፈልጎ ከያዘ በኋላ ያስረውን እቃ ከመስኮቱ ሥር አስቀመጠው:: ወደ አልጋው ተመልሶ ያስቀመጠውን እቃ አነሳ:: እቃው ከአንድ ጫፍ እንደ ጦር የሾለ፤ ከሌላው ጫፍ ቋር ያለው ወፍራም ብረት



ነበር:: በዚያ ጨለማ ብረቱ ለምን ሥራ እንደተዘጋጀ ለመለየት አስቸጋሪ ነበር:: ዱላ ነው ወይስ እቃ ማንሻ? አይታወቅም:: ቀን እንኳን ቢሆን የማዕድን ሠራተኞች መቆፈሪያ ነው ለማለት ያስችላል:: በዚያን ጊዜ ቱሉን ከተባለ ቦታ አካባቢ በሚገኙ ከፍተኛ ኮረብታዎች ላይ ድንጋይ እንዲፈልጡ የተፈረደባቸው ወንጀለኞች ይቀጠሩ ነበር:: ወንጀለኞቹ ብዙውን ጊዜ የዚያን ዓይነት ብረት የመሰለ መፍለጫ ይይዛሉ::

ዣን ቫልዣ ያን ብረት በቀኝ እጁ ያዘ:: ትንፋሹን ውጦ በዝግታ ተራመደ:: ወደ ጳጳሱ መኝታ ቤት አመራ:: ወደ በሩ ሲጠጋ አለመቆርቆሩን ተመለከተ:: «አባታችን በራቸውን ሳይቆልፉ ነው የሚተኙት» አለ በልቡ::

ዣን ቫልዣ ጆሮውን አቅንቶ አዳመጠ:: ድምፅ የሚሉት ነገር የለም:: በሩን ከፈት አድርጎ ሲፈራ ሲቸር በጣቶቹ ጫፍ ቀስ ብሎ ገፋው:: ጥንቃቄው ከድመት ይበልጣል:: በሩ ምንም ድምፅ ሳያሰማና ለመንቀሳቀሱ እንኳን በሚያጠራጥር ሁኔታ በዝግታ በመገፋቱ ከመጀመሪያው ይበልጥ ጥቂት ከፈት አለ::

ለጥቂት ጊዜ ከበሩ አጠገብ ቆም አለ:: አሁን ግን በይበልጥ ድፍረቱ ስለተሰባሰበለት ከቀድሞ በበለጠ ጉልበት በሩን ገፋ አደረገው:: በዚህ ጊዜ የበሩ ማያያዣ የዛገ ብረት ረዘም ያለ የሚሰቀጥጥ ድምፅ አሰማ::

ልቡ የተሰነጠቀ መሰለው:: እንደ እንጨት ደርቆ ከቆመበት ሐውልት ይመስል ሳይንቀሳቀስ ለጥቂት ጊዜ ተገተረ:: ለመንቀሳቀስ አቅም አነሰው፤ ድፍረትም አልነበረውም:: ጥቂት ደቂቃዎች አለፉ:: በሩ ወለል ብሎ ተከፍቷል:: ወደ ክፍሉ ተመለከተ:: የተንቀሳቀሰ ነገር የለም:: አዳመጠ፤ የሚንቀሳቀስ ወይም ድምፅ የሚሰጥ ነገር አሁንም ከጆሮው አልገባም:: የበሩ ድምፅ ማንንም አልቀሰቀሰም ማለት ነው::

የመጀመሪያው አደጋ አለፈ:: ልቡ ግን በጣም ፈርቷል፤ ሆኖም አላወላወለም:: የፈለገውን ተሉ ለመጨረስ ቁርጥ አሳብ አደረገ:: በአንድ እርምጃ ከክፍሉ ውስጥ ገባ:: ክፍሉ ውስጥ ጸጥታ ሰፍኖበታል:: ዣን ቫልዣ ከወንበርና ከጠረጴዛ ጋር እንዳይጋጭ እየተጠነቀቀ ወደፊት ተራመደ:: ጳጳሱ ከክፍሉ ውስጥ ጥግ ይዘው ተኝተው በኃይል ሲተነፍሱ አዳመጠ:: በድንገት ቆም አለ:: ከጳጳሱ አልጋ አጠገብ ደርሷል:: ቶሉ የደረሰ መሰለው::

አንዳንድ ጊዜ ተፈጥሮ የምንሠራውን ሥራ ለማራገብ ከእኛ ጋር ታብራለች:: ለግማሽ ሰዓት ያህል ደመና ጨረቃን በመጋረድዋ አካባቢው ጨልሞ ነበር:: አሁን ግን ልክ እንደተመካከረ ሰው ዣን ቫልዣ ከጳጳሱ አልጋ አጠገብ እንደቆመ ደመና ለጨረቃ ቦታዋን ለቀቀች:: የጨረቃ ብርሃን በመስኮት በኩል ዘልቆ በመግባት ከጳጳሱ የገረጣ ፊት ላይ አበራ:: ጭልጥ

አድርጎ እንቅልፍ ወስዷቸዋል:: የሌሊቱ ብርድ ከባድ ስለነበር ወፈር ያለ የሌሊት ልብስ ለብሰው በጀርባቸው ተዘርረው ነው የተኙት:: ስንት ደግ ሥራ የሠራው ታማኙና ነዳያን የሳሙት እጃቸው ካልጋው ጠርዝ አልፎ ወደመሬት ተንጠልጥሎአል:: ሌላው እጃቸው ከደረታቸው ላይ በማረፉ የጵጵስና ቀለበታቸው ያበራል:: እዚያ ተጋድመው ሲያይዋቸው መላ አካላቸው የተሰፋ፤ የደስታና የእርካታ ማኅደር እንደሆነ ይናገራል:: በቃላት ለመግለጽ የሚያዳግት የማይታይ ብርሃን ከግንባራቸው ላይ አርፎአል::

የጨረቃው በሰማይ ላይ መንጣለል፤ የምድር በከፊል የተኛች መምሰል፤ የግቢው አትክልት እርጭ ማለትና የቤቱና የዚያች ሰዓት ፀጥታ እኚህ መለኮት የቀረባቸውን ሰው «አክብሩ አትድፈሯቸው» የሚያሰኝ ነበር:: ዓይናቸውን ጨፍነው እንደተኙ የነበራቸው ግርማ ሞገስና ለተሰፋ ምንጭ የሆነውና በጨርቅ ያልተሸፈነው ግንባራቸው ሲያዩት በፍርሃት የሚያርበደብድ ነበር::

በዚህ የተነሣ ዣን ቫልዣ በፍርሃት ተውጦና ሐውልት መስሎ ድምፅ ሳያሰማ ከጥላ ሥር ባለቋሩን ብረት ይዞ ከእኚህ ደግ ሰው ፊት ቆሞአል:: በሕይወቱ እንደዚያ ያለ ሁናቴ ገጥሞት አያውቅም:: ይህም በይበልጥ እንዲፈራ አደረገው:: የተብከነከነና የተቅበጠበጠ ሕሊና ክፉ ተግባር ለመፈጸም ከዚያ ቆሞ ሳለ ንጹሑ ነፍስ እንቅልፍ ወስዶት ከእዚያ ተኝቷል::

ጥቂት ቆሞ ሁኔታውን ከተመለከተ በኋላ በግራ እጁ ቀስ ብሎ ቆቡን አወለቀ:: ከዚያም ቆቡን ለማውለቅ ያነሳውን እጁን አሁንም በዝግታ አውርዶ እንደገና ዣን ቫልዣ ማሰላሰል ጀመረ:: ቆቡን በግራ እጁ፣ የብረት ዱላውን በቀኝ እጁ ይዟል:: ጳጳሱ ግን ከተኙበት ነቅነቅ አላሉም::

በድንገት ዣን ቫልዣ ቆቡን አጠለቀ:: ከዚያም ወደ ጳጳሱ ሳያይ ከአልጋቸው አልፍ ብሎ ወደ ነበረው ቡፌ ሄደ:: የቡፌው ቁልፍ ከላዩ ላይ ስለነበር ከፈተው:: በመጀመሪያ ያየው እነዚያን ከብር የተሠሩ የሚያማምሩ ማህኖችን ነበር:: ሳህኖቹን ከንጭልፋው ይዞ ወደ በሩ አመራ:: የእግሩ ኮቴ ይሰማል በማለት ብዙም ሳይጨነቅ በኃይል እየተራመደ ከክፍሉ ወጥቶ ሄደ:: የብር እቃዎቹን ከአቁማዳው ውስጥ ከተተ:: በአትክልቱ መካከል አልፎ ሄዶ አጥሩን በመዝለል ከግቢው ከወጣ በኋላ መንገዱን ቀጠለ::

❀❀❀



# ፯

በጠዋት ፀሐይ እንደ ወጣች ጳጳሱ ከአትክልት ውስጥ ይንሸራሸራሉ:: መዳም ማግልዋር እየሮጡ መጡ::

«አባታችን ሰውዬው ሄዷል፤ እነዚያ የብር ሣህኖችም ተሠርቀዋል::»

ሴትዮዋ ይህን ሲናገሩ ከአትክልቱ ውስጥ የእግር ኮቴ ተመለከቱ:: ኮቴውን ተከትለው ግምቡን ሲያዩ ከአንድ ፊት መሸረፉን ተገነዘቡ::

«አባታችን እዩ፤ በዚያ በኩል ነው የወጣው:: በአጥር ዘልሎ ነው የሄደው:: ምን ዓይነት ቀበኛ ነው:: ሣህኖቻችንን ሠርቆ ነው የሄደው::»

ጳጳሱ ለጥቂት ጊዜ ዝም አሉ:: ከዚያም አንገታቸውን ቀና አድርገው ሴትዮዋን እየተመለከቱ «ጥንትም ቢሆን እኮ ሣህኖቹ የእኛ ነበሩ እንዴ?» ሲሉ ጠየቁ::

መዳም ማግልዋር አልመለሱም:: ለጥያቄያቸው መልስ ስላላገኙ ጳጳሱ ንግግራቸውን ቀጠሉ::

«መዳም ማግልዋር፤ እነዚህን ሣህኖች የነዳያን ሀብት ሆነው ሳለ ለረጅም ጊዜ ያለ አግባብ አስቀመጥናቸው:: ይህ ሰው ማነው? ከነዳያን አንዱ ነው::»

«ይገርማል» አሉ መዳም ማግልዋር:: «እኔም ሆንኩ እህትዎ ግድ የለንም፤ ለእኛ እንደሆነ ሴቶች እንደመሆናችን ለውጥ አያመጣም:: ግን ለብፁዕነትዎ ገበታ ሲቀርብ አሁን የትኛው ሳህን ሊቀርብ ነው?»

ጳጳሱ በመገረም ሴትዮዋን አተኩረው ተመለከቱ::

«እንዴት እኮ! የቆርቆሮ ሣህን ቢሆን እንኳን! ሌላ ሣህን የለንም ማለት ነው?» ሲሉ ጠየቁ::

መዳም ማግልዋር ትከሻቸውን ነቀነቁ::

«የቆርቆሮ ሣህን እኮ ሽታ ያመጣል::»

«እንግዲያውማ ከብረት የተሠራ ሣህን ካለ እርሱ ሊሆን ይችላል::»

መዳም ማግልዋር ፈገግ ብለው «እሱም ቢሆን ብረት ብረት ማለቱ ይቀራል!» አሉ::

«እንግዲያውማ» አሉ ብፁዕነታቸው፤ «የእንጨት ወይም የሸክላ ሣህን መፈለግ ነዋ!»

ከጥቂት ጊዜ በኋላ በአለፈው ሌሊት ዣን ቫልዣ አብሮ ከቀረበበት

ጠረጴዛ ላይ ቁርስ ተዘጋጀ። ቁርስ እየበሉ ምንም ዓይነት አስተያየት ሳልሰጡት እህታቸውና ለሚያጉረመርሙት ለመዳም ማግሬዋር ዳቦ ሸይ ውስጥ ነበር ለመብላት ማንኪያ ወይም ሹካ የማያስፈልግ መሆኑን በመግለጽ ላት እያሉ ይናገሩ። ወዲያው እህትና ወንድም ቀና ብለው ሲተያዩ በር ይንኳኳል።

«ይግቡ» አሉ ጳጳሱ።

በሩ ተከፈተ። ሦስት የሚያስፈሩና ለቤቱ እንግዳ የሆኑ ሰዎች ገቡ። ሰዎቹ የአራተኛ ሰው አንገት ጨምድደው ይዘዋል። ሦስቱ ሰዎች ፖሊሶች ሲሆኑ አራተኛው ሰው ዣን ቫልዣ ነበር።

አዛዡ ወደፊት ቀደም ቀደም ብሎ በወታደር ደምብ መሠረት ለጳጳሱ የክብር ሰላምታ ሰጠ።

«ብፁዕነትዎ...» አለ።

እስከዚያች ደቂቃ ድረስ አኩርፎ ዝም ያለውና ያቀረቀረው ዣን ቫልዣ ያዛዡን ንግግር አቋርጦ ጣልቃ በመግባት እፍረት እየተሰማው አንገቱን ቀና አደረገ።

«አባታችን፣ የደብር አለቃ ብቻ አይደሉማ!» ሲል ተናገረ።

«ዝም በል!» አለ ፖሊሱ። «አባታችን እኮ ናቸው። የብፁዕነታቸውን ማዕረግ እንኳን አታውቅም?»

ብፁዕነታቸው እድሜያቸው በፈቀደው መጠን በቶሎ ከገበታው ብድግ ብለው ወደ ሰዎቹ ጠጋ አሉ።

«መጣህ» አሉ ወደ ዣን ቫልዣ እየተመለከቱ። እንደገና በመገናኘ ታችን ደስ ብሎኛል። ግን የሻማ ማብሪያዎችንም ጭምር ሰጥቼህ አልነበረም እንዴ፣ ምነው ተውካቸው? እነርሱም እኮ ከንጹህ ብር የተሠሩ ናቸው። እስከ 200 ፍራንክ ያወጡልሃል። ከሣህኖቹ ነጥለህ ምነው አስቀረሃቸው? ሲሉ ጠየቁት።

ዣን ቫልዣ አፉን ከፍቶ ብፁዕነታቸውን አፍጥጦ ተመለከተ። የሚሰማው ነገር እውነት መሆኑን ማመን አቃተው።

«አባታችን» አለ አዛዡ፤ «እንግዲያውስ ይህ ሰው ያለው ትክክል ነው ማለት ነዎ? እኛ ስንይዘው እንደገመገምነው የሚሸሽ ሰው ዓይነት መስሎን ነበር። ስለዚህ ተጠራጥረን ያዝነው። እነዚያን የብር እቃዎች መያዙ ደግሞ በይበልጥ አጠራጠረን።»

«እና ተነጋግራችኋላ!» አሉ ጳጳሱ ፈገግ ብለው፤ «ትናንት ሌሊት



ካስጠጉት ከአንድ ሽማግሌ መነኩሴ የተሰጠው እቃ ለመሆኑ ገልጾላችኋል! እናንተ ግን በመጠራጠር ይዛችሁት መጣችሁ፣ ተሳስታችኋል። እቃው የራሱ ነው።»

«እንዲህ ከሆነማ ሰውዬን በነፃ ልንለቅቀው እንችላለን» አለ አዛዡ።

«ያለ ጥርጥር» ሲሉ ብፁዕነታቸው መለሱ።

ፖሊሶቹ ዣን ቫልዣን ለቀቁት። ወደኋላ አፈገፈገ።

«አሁን በእርግጥ በነፃ ሊለቁኝ ነው?» ሲል ዣን ቫልዣ እጅግ በጣም ዝቅተኛ በሆነ ድምፅ አጉረመረመ። ቅዠት መሰለው እንጂ በውኑ እንደሆነ አላመነም።

«አዎን! ልትሄድ ትችላለህ፣ ነገር አይገባህም» አለ ፖሊሱ።

«ወዳጄ» አሉ ጳጳሱ፣ «ከመሄድህ በፊት እነዚያም የሻማ ማብሪያዎች የአንተ ስለሆኑ ውሰዳቸው።»

ጳጳሱ ወደ ምግብ ጠረጴዛ ሄደው የሻማ ማብሪያዎችን አምጥተው ለዣን ቫልዣ ሰጡት። ሁለቱ ሴቶች ተገርመው ከእዚያው ከገበታ ላይ አቀርቅረው ቀሩ። ቃል አልተነፈሱም።

ዣን ቫልዣ ሰውነቱ ርዶ መቆም ተሳነው። የሻማ ማብሪያዎቹን ተቀበለ። ፊቱ የአውሬ መሰለ።

«አሁን» አሉ ብፁዕነታቸው «በሰላም መሄድ ትችላለህ።» ከዚያም ብፁዕነታቸው ፊታቸውን ወደ ፖሊሶቹ አዙረው፣ «ልጆቼ፣ ወደ ሥራችሁ ልትመለሱ ትችላላችሁ» አሉ። ፖሊሶቹ ወጥተው ሄዱ።

ዣን ቫልዣ ራሱን ስቶ ከመሬት እንደሚዘረር ሰው ተንገዳገደ፣ ግን አልወደቀም። ጳጳሱ ወደ እርሱ ጠጋ ብለው ዝቅ ባለ ድምፅ የሚከተለውን ተናገሩ።

«አትርሳ! ገንዘቡን እውነተኛና ታማኝ ሰው ለመሆን እጠቀምበታለሁ ብለህ ቃል የገባኸውን እስከ እድሜ ልክህ እንዳትረሳ።»

ዣን ቫልዣ መቼ ቃል እንደገባላቸው ማስታወስ አቅቶት በመደናገር ዝም ብሎ ቆመ። ጳጳሱ «ቃል የገባኸውን አትርሳ» በማለት አጥብቀው ጠይቀውታል። ንግግራቸውን ቀጠሉ። «የእኔ ልጅ ዣን ቫልዣ፣ ከእንግዲህ አንተ ለጥፋት ዓለም ሳይሆን ለደግነት የተመረጥህ ነህ። ነፍስህን ነው የምገዛልህ። የአንተን ነፍስ የምሰጠው የሁሉም በላይ ለሆነው ለአንድ አምላክ ነው።»

ዣን ቫልዣ አገር ጥሎ እንደሚሸሽ ሰው እግሩ እውጪ በማለት

ከተማውን ጥሎ ወጣ። ከተማውን ለቅቆ ገጠር እስኪገባ ድረስ እየተጣራ ነበር የሚሄደው። ወዴት እንደሚሄድ ሳያስተውል መንገድ እንደመራው ዝም እያለ ተጓዘ። ከነጋ ጀምሮ እህል አልቀመሰም። ሆኖም የረሃብ ስሜት አልተሰማውም። ቁጣ ቁጣ ብሎታል። በማን ላይ ወይም በምን ምክንያት እንደተቆጣ ግን አያውቅም። የሚቀጥለው ምን ይሆን ሲል ራሱን ጠየቀ። የገጠር አየር የልጅነት ጊዜውን አስታወሰው። የልጅነት ዘመኑን ካስታወሰ በጣም ቆይቶ ነበር። ከዚያም ብዙ ሃሳቦች ተፈራረቁበት።»

❀❀❀

፮

ፀሐይ አሽቆልቁላ ገብታ ከአድማስ ውስጥ ልትገባ ስትል ዣን ቫልዣ እልም ካለ ጫካ ውስጥ ከአንዲት ጉብታ ላይ ቁጭ ብሎአል። የአልፐስ ተራራ በሩቁ ይታያል። ከጫካው ወጣ እንዳለ አንድ ቀጭን የእግር መንገድ አለ።

ከዚህ ቁጭ ብሎ ሲያሰላስል ደስ የሚል ድምፅ ይሰማል። ፊቱን ቢያዞር ወደ አሥራ ሁለት ዓመት የሚሆነው ልጅ እየዘመረ ወደ እርሱ ይመጣል። ልጁ በጭንቅላቱ ላይ ሣጥን መሳይ ነገር ተሸክሟል። ልጁ ጥቂት ከተራመደ በኋላ ቆም ብሎ በእጁ የያዘውን ሣንቲም ወደ ሰማይ እያጎነ ይጫወታል። የልጁ ሀብት ምናልባት ይኸው ነጭ ሽልንግ ብቻ ሳይሆን አልቀረም።

ዣን ቫልዣ ከተቀመጠበት ሲደርስ የሰውዬው ከእዚያ መኖር ሳይገነዘብ ቆም አለ። እንደ ልማዱ ሣንቲሙን ወደ ሰማይ አጎነ። ሣንቲሙ አምልጦት ከመሬት ሲወድቅ ዣን ቫልዣ ወደ ተቀመጠበት በረረ። ዣን ቫልዣ ሽልንጉን በእግሩ ረግጦ ያዘበት። የልጁ ዓይን ሣንቲሙን ተከትሎ ስለሄደ የት ላይ እንዳለ ያውቃል። ልጁ አልፈራም፤ በቀጥታ ወደ ሰውዬው ሄደ።

«ጌታዬ ገንዘቤን» አለ ልጁ የዋህነትና ድንቁርና በተሞላበት አንደበት።

«ስምህ ማነው?» ሲል ዣን ቫልዣ ጠየቀው።

«ትንሹ ዠራቬ ነው ጌታዬ።»

«ቶሎ ከዚህ ጥፋ» አለው ዣን ቫልዣ።

«ፍራንኬስ?» ሲል ልጁ ጠየቀ።



ዣን ቫልዣ እንዳቀረቀረ ቀረ።

«ገንዘቤን» አለ ልጁ እምባ እየተናነቀው። «ሽልንጌን!»

ዣን ቫልዣ ምንም ነገር እንዳልሰማ ሰው ዐዮ አለ። ልጁ የሰውዬውን ሸሚዝ ኮሌታ በአንድ እጁ ያዘ። በሌላው እጁ ሣንቲሙን ለማስለቀቅ የሰውዬውን እግር ለማንሳት ሞከረ።

«ገንዘቤን አፈልጋለሁ፤ ሽልንጌን!» ብሎ ከሙሉ በኋላ ትንሹ ዠራቬ ማልቀስ ጀመረ። ዣን ቫልዣ አንገቱን ቀና አደረገ። ከተቀመጠበት ግን አልተነሳም። ፊቱ በሐሳብ የተዋጠና የተጨነቀ ይመስላል። በመጨረሻም ልጁን አትኩሮ አየው። ዱላውን ሳብ አድርጎ «አንተ ማነህ? እህ! ምንድነው የምትፈልገው? እስካሁን አልሄድክም እንዴ» ሲል በሚያስፈራ ድምፅ ጮኸበት። ሣንቲሙን እንደረገጠ ከመቀመጫው ብድግ ብሎ «ራስህን ብትጠብቅ ይሻልሃል» አለው።

ልጁ በፍርሃት ተውጦ ቀና ብሎ አየው። ሰውነቱ ይንቀጠቀጥ ጀመር። ወዲያው ከጥቂት ሰከንድ መርበትበት በኋላ ልጁ እግሩ እውጪ ብሎ ሸመጠጠ። ዞር ብሎ ለማየት ወይም ጩኸት ለማሰማት እንኳን አልደፈረም። ሆኖም ጥቂት እንደተጓዘ ትንፋሽ አጥሮት ቆም አለ። ግን ብዙ አልቆመም፤ መንገዱን ቀጠለ።

ፀሐይዋ ጠለቀች። ዣን ቫልዣ ከተቀመጠበት አካባቢ ብርሃን ለጨለማ ሥፍራዋን ለቀቀች። ቀኑን ሙሉ ምግብ የሚሉት ነገር አልቀመሰም። ምናልባትም ትኩሳት እንደተከሰተ ብጤ ሳይሞክረው አልቀረም።

ልጁ ከሄደ ጀምሮ ከተቀመጠበት ንቅንቅ አላለም። በኃይል ነው የሚተነፍሰው። ከተቀመጠበት ጥቂት ራቅ ብሎ ከነበረው የሸክላ ስባሪ ገል ላይ ዓይኑን ተከለ። ስለገሉ ይመራመር ጀመር። ግን በድንገት መላ ሰውነቱ ተንቀጠቀጠ። የሌሊቱ ቁር እየተሰማው ሄደ።

ቆቡን ሳብ አድርጎ ግንባሩን ሸፈነ። የሸሚዙን አዝራር ለመቆለፍ ጣቶቹ አዝራር ፍለጋ ላይ ታች አሉ። ብድግ ብሎ ወደፊት ራመድ ካለ በኋላ መለስ ብሎ ዱላውን ለማንሳት ጎንበስ አለ።

በእግሩ ረግጦ ይዞት የነበረው ሽልንግ በማብረቅረቁ ዓይኑ ወደዚያ ተሳበ። ኮረንቲ እንደያዘው ሰው ተሸማቀቀ። «ምንድነው ነገሩ?» ሲል ጥርሱን በማፋጨት ራሱን ጠየቀ። እንደገና ወደኋላ መለስ ብሎ ሣንቲሙን በእግሩ በመርገጥ ሸፈነው። ሣንቲሙ ዓይን አብቅሎ የሚያየው መሰለው።

ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ እግሩን መነጨቀና ጎንበስ ብሎ ሣንቲሙን አነሳ። ቀና ብሎ አካባቢውን ተመለከተ። ጋራውና ሸንተረሩ ሁሉ የሚያየው

ስለመሰለው በፍርሃት ተውጦ መጠጊያ እንደምትፈልግ ዱኩላ ዓይኑ በፍርሃት ተቅበዘበዘ:: ከቆመበት ተገትሮ ቀረ::

ምንም ነገር አላየም:: ጊዜው እየጨለመና አየሩ እጅግ እየቀዘቀ ሄደ:: ሰማዩ በጭጋግ ተሸፈነ::

«ወይ ጣጣ» ሲል ልጁ በሄደበት አቅጣጫ ጉዞውን ቀጠለ:: እን ሰላሳ እርምጃ ያህል እንደተራመደ ቆም አለ:: አካባቢውን ተመለከተ:: ምንም ነገር የለም::

ድምፁን እጅግ ከፍ አድርጎ «ዡራሺ» ሲል ተጣራ:: ከዚያም ድምፁ አጥፍቶ አዳመጠ:: መልስ አላገኘም::

አገሩ ጭር ያለና ጭጋጋም ቢሆንም አካባቢው በግልጽ ይታያል:: ከዝምታና ከራሱ ጥላ በስተቀር የሚንቀሳቀስ ፍጡር ጨርሶ አልነበረም::

ዣን ቫልዣ መንገዱን ቀጠለ:: የሚወስደውን እርምጃ ፍጥነ በመጨመር እንደ መሮጥ አለ:: አልፎ አልፎ ቆም እያለ በሚያስፈራ ሻካ ድምፅ «ዡራሺ» ሲል እንደገና ተጣራ:: እንደ እውነቱ ከሆነ ልጁ ቢሰማው እንኳን በፍርሃት ስለሚዋጥ ይደበቃል እንጂ መልስ አይሰጠውም:: ነገ ግን ልጁ በርግጥም በጣም ርቆ ሄዷል::

ዣን ቫልዣ እንደገና ልጁ በሄደበት አቅጣጫ መሮጥ ጀመ እየተገላመጠ! እየጮኸ! እየተጣራ ብዙ ተጓዘ:: ግን ማንንም አላገኘ በደረቱ ተንፏቅቆ የሚሄድ ወይም ድምፁን አጥፍቶ ያደፈጠ እየመሰለ ከአንዴም ሁለቴ! ከሁለቴም ሦስቴ መንገዱን ለቅቆ ወደ ጥሻው ዞር እ ተመለከተ:: ግን ሰው የመሰለው ነገር ጠጋ ሲል ቁጥቋጦ ወይም ድንጋ ሆኖ ያገኘዋል:: በመጨረሻ ሦስት መንታ መንገዶች ከሚገናኙበት ደረ ከመሐል መንገድ ላይ ቆመ:: ጨረቃዋ ብቅ ብላለች:: ለማየት እስከ ድረስ አርቆ ተመለከተ:: «ዡራሺ! ትንሹ ዡራሺ! ዡራሺ» በማ ሦስት ጊዜ ድምፁን ከፍ አድርጎ ተጣራ:: ድምፁ የገደል ማሚቶ እን ሳይሰማ ከጭጋጉ ውስጥ ተውጦ ቀረ:: «ትንሹ ዡራሺ» ሲል ዝግ በደከመ ድምፅ አጉረመረመ:: ያ የመጨረሻው ሙከራ ነበር:: በዓ የማይታይ ኃይል በዱላ እንደመታው ሰው በድንገት እግሩ ተሳስሮ ጉል አጥፍጥፍ አለበት:: ፀጉሩን በእጁ ጨብጦና ፊቱን ጉልበቱ ላይ አ ከቋጥኝ ድንጋይ ላይ በመቀመጥ «ምን ዓይነት እድለቢስ ሰው ነኝ» ጮኸ:: ልቡ እያበጠ ሄደ:: ምርር ብሎ አለቀሰ:: ከአሥራ ዘጠኝ ዓ ወዲህ ሲያለቅስ የመጀመሪያው ነበር:: ዣን ቫልዣ ብዙ አለቀሰ:: ከሕ መባቱና ከሴቶች መርበትበት ይበልጥ በፍርሃት ተውጦ ከዓይኑ የ እምባ የወጣ እስኪመስለው ድረስ በማልቀስ እንጆቱን እርር ድብን አ



እያለቀሰ ሳለ ከሕሊናው ውስጥ የነበረው ብርሃን እየፈካ ሄደ:: የተለየ ብርሃን ነበር:: ያ ብርሃን አሳየው! አስፈራራው:: ያለፈው የሕይወቱ ዘመን! የመጀመሪያው ወንጀሉ! የረጅም ጊዜ ስቃዩ! ጨካኝ ዓለም! የደነደነው ልቡ! ከእስር ቤት ማምለጡ! ከጳጳሱ ቤት በእርሱ ላይ የደረሰው! የመጨረሻው አሳፋሪ ድርጊቱ! ከሕፃን ልጅ ገንዘብ መዝረፉ! ጳጳሱ ይቅርታ ካወረዱለት በኋላ የተፈጸመ አስቃቂና አስፈሪ ወንጀል መሆኑ! ይህ ሁሉ ከዓይነ ልቦናው ውስጥ እየተመላለሰ ከዚያ በፊት ታይቶት በማይታወቅ ዓይነት ቁልጭ ብሎ ታየው:: ያለፈውን የሕይወቱን ምዕራፍ በአሳብ በተመለከተው ጊዜ እጅግ አስቀያሚና አስከፊ መሆኑን ተረዳ:: የነፍሱንም መኩነን አልተጠራጠረም:: ሆኖም ነፍሱ የተስፋ ጭላንጭል ብርሃን ጨርሶ የተለየው አልነበረም:: ቢሆንም ከዚያ የተስፋ ጭላንጭል ባሻገር ይመለከተው የነበረው የሰይጣን ጥላ ነበር::

ይህም በመሆኑ ከማልቀስ አልተገታም:: ከልቅሶው በኋላ ምን ሆነ? ምን አደረገ? የት ሄደ? ማንም አላወቀም:: ነገር ግን በዚያን እለት ምሽት በዚያ በኩል ያለፈ ባለጋሪ ከአኚያ ደግና ቸር ጳጳስ ቤት በራፍ ከመንገዱ ጠርዝ ፊቶት ብሎ ጥላ ስር ከሌሊቱ ዘጠኝ ሰዓት ገደማ ተንበርክኮ በስሜት ይጸልይ የነበረ ሰው ማየቱለን ተናግሯል::

❀❀❀

## ምዕራፍ ሦስት

# አንዳንዴ ኃላፊነትን ከመሸከም አሳልፎ መስጠት

በ18ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ ፓሪስ አጠገብ ከሚገኘው ሞንትፈርሜ ከተባለ ሥፍራ አንድ አነስተኛ ሆቴል ቤት ነበር:: ዛሬ ግን የለም:: ሆቴል ቤቱ ዘቴናድዩስ የተባሉ ባልና ሚስት ንብረት ሲሆን የሚገኘው ቡላንዣ ከተባለ ተጭን መንገድ ላይ ነበር:: ከቤቱ በራፍ ላይ ስዕል ተንጠልጥሎአል:: ስዕሉ ላይ ሜዳሊያ የተሰካለትና በደም ተበክሎ የተበጫጨቀ የጀኔራል ልብስ የለበሰ ሰው ሸክም ተሸክሞ ነው የሚታየው:: በተጨማሪም ከምስሉ ባዶ ሥፍራ ላይ ጭስ በብዛት አለ:: የሚያመለክተው የጦር ሜዳን ሳይሆን አይቀርም:: ከምስሉ ስር «የዋተርሉ ጦር ሜዳ ጀግናው የሣምሳ አለቃ» የሚል ጽሑፍ ተጽፎበታል::

ከዚህ ሆቴል ቤት በራፍ ጋሪ ቆሞ ማየት አዲስ ነገር አልነበረም፡፡ ሆኖም«ከዋተርሉ የጦር ሜዳ ጀግናው የሃምሳ አለቃ» ሆቴል ቤት በራፍ የተሰበረ ጋሪ መንገድ ዘግቶ ሲቆም በወትር የሚታይ ትርኢት አይደለም፡፡ ጊዜው የዐደይ ወራት ሲሆን ዓመተ ምህረቱ 1818 ዓ.ም ነው፡፡ የጋሪው መንገድ ዘግቶ መቆም፣ ያን የመሰለ ስዕል ከዚያ ቤት በራፍ መስቀል በዚያ ያለፈ የማንኛውም ሰጓሊ ዓይን የሚማርክ ትርዒት ነበር፡፡

ጋሪው ትላልቅ ግንዲላዎችን ጭኖአል፡፡ ታዲያ ይህ ጋሪ ከዚህ ስፍራ ምን ይሠራ ነበር የሚል ጥያቄ ቢነሳ «ከዚያ የተገተረውማ መንገድ ለመዝጋትና የትጉህ ሠራተኞችን ተግባር ለማደናቀፍ ነው» የሚል ትርጉም ሊያሰጥ ይችላል፡፡

ከጋሪው የእቃ መጫኛ ሥር የተንጠለጠለው ወፍራም ሰንሰለት መሬት ሊነካ ምንም አልቀረው፡፡ አንዲት ሁለት ዓመት ተመንፈቅ የሚሆናት ልጅ ሌላ ዓመት ከስድስት ወር የሚሆናትን ሕፃን ጭንዋ ላይ አሳርፋ ከሰንሰለቱ ላይ ተቀምጣለች፡፡ ልጆቹ ጅዋጅዋ ላይ እንደወጡ ደስ ብሏቸዋል፡፡ አንዲት ሴት አቀማመጣቸውን አይታ «ልጆቹ መጫወቻ አገኙ» በማለት ደስ እንደሚላት ማንኛዋም እናት በማተኮር ታያቸዋለች፡፡ አተኩሮ ለተመለከታት አንጀት የምትበላ፤ አንዴ እንኳን ለማየት የምትቀፍና ኑሮ እጅግ ያጎሳቆላት ሌላ ሴት ከበራፉ አጠገብ ተቀምጣለች፡፡ ልጆቹ ደስ ብሏቸው ሲጫወቱ «ምናልባት ፈረሱ ደምብሮ ይጉዳቸው ይሆን» እያለች የመጀመሪያዋ ሴት አሁንም እንደማንኛውም እናት ማሰብዋ አልቀረም፡፡ ሰንሰለቱ በተንቃነቀ ቁጥር ሲጥጥ እያለ ይጮሃል፡፡ ድምፁ ሕፃናቱን አልረበሻቸውም፡፡ የማታ ጨረር ከልጆቹ ላይ በማረፉ ልብ ብሎ ለተመለከታቸው ዓይንን ይማርካል፡፡

የልጆቹ እናት በድንገት ድምፅ ትሰማለች፡፡ «እሜቴ ደስ የሚሉ ልጆች ነው ያሉዎት!»

ከምግብ ቤቱ በራፍ የተቀመጠችው ሌላዋ ሴትም ልጅ ታቅፋ ነበር፡፡ ከወፍ የሚመስል እቃ በጀርባዋ አዝላለች፡፡ እርስዋም የታቀፈቻት ልጅ ሁለት ወይም ሦስት ዓመት ቢሆናት ነው፡፡ በአለባበስ ከሁለቱ ልጆች ምንም ያህል አትለይም፡፡ ሻሽ መሳይ ጨርቅ አስራለች፡፡ የተበጫጨቀ ቀሚስዋ ቀዳዳው እስከጭንዋ ሊደርስ ምንም አልቀረው፡፡ ሆኖም ጤነኛ ነበረች፡፡ መልክዋ ድምቡሽቡሽ ያለ ስለሆነ ንክሱኝ፣ ንክሱኝ ትላለች፡፡ ዓይኖችዋ ትላልቅ ስለነበሩ እንቅልፍ ቢወስዳትም ሙሉ ለሙሉ አልተከደኑም፡፡ ለስለስ ካለው የእናትዋ ክንድ ላይ ተመችቶአት ስለተኛች እንቅልፍ ሳይጠግብ ቢቀሰቅሱት እንደማይሰማው እንደማንኛውም ሕፃን እርስዋም ቢቀሰቅሱዋት እንኳ አትሰማም፡፡



እናትዮዋ ሲያዩዋት የተከፋች ምስኪንና ከተማ ሥራ ፍለጋ የመጣች የገጠር ሴት ለመሆንዋ ታስታውቃለች፡፡ በእድሜ ልጅ ናት፡፡ ተፈጥሮ ውበት ቢቸራትም በዚያ ሁኔታዋ ውበትዋ ጎላ ብሎ አይታይም፡፡ በጉርዋ ዞማ እንደሆነ ቢያስታውቅም ተንጨፍሮአል፡፡ የተቀዳደደ ሻሽዋ ተፈትቶ ሲወድቅ ብሎ ከወደኋላዋ ተንጠልጥሎአል፡፡ የደላው ሲስት ነጭ ጥርሱን ያሳያል እንጂ የተከፋ ስለማይስቅ ስለጥርሶችዋ ለመናገር አይቻልም፡፡ ለረጅም ጊዜ ለማልቀስዋ ዓይኖችዋ ይመሰክራሉ፡፡ ገርጥታለች፤ ሰውነትዋ በመዛሉ የደከማት ለመሆኑ ያስታውቃል፡፡ ምናልባትም ሳትታመም አልቀረችም፡፡ ጭንዋ ላይ የተኛችዋን ልጅ አትኩራ በፍቅር ዓይን ትመለከታታለች፡፡ ልጅዋን ደግፋ የያዘችበት እጅ ሲታይ በሥራ ብዛት ለመሻከሩ ጉልህ ነው፡፡

ጠቅላላ ሁኔቷ ሲታይ ሩህሩህ ልብ ያላቸው ሁሉ የማያልፍዋት ዓይነት ሰለነበረች አንጀት ትበላለች፡፡ በይበልጥ የሚያሳዝነው ግን ማን ትሁን፤ ከየት ትምጣ ማንም አለማወቁ ነው፡፡ እርስዋም ራስዋ ብትሆን አባትዋና እናትዋ እነማን እንደሆኑ ማለት ማን እንደወለዳት አታውቅም፡፡ ስምዋ ፋንቲን ይባላል፡፡ ቤተሰብ ስላልነበራት የአባት ስም የላትም፡፡ የክርስትና ስምም አልወጣላትም፡፡ ምክንያቱም በዚያ አካባቢ ቤተክርስቲያን ምን እንደሆን አይታወቅም፡፡ ፋንቲን ብሎ ስም ያወጣላት በዚያ ሲያልፍ ያገኛት መንገደኛ ነው ይባላል፡፡ ይህ ሰው ይህችን ሕፃን መንገድ ወድቃ ዝናብ ሲዘንብባት ነው ፋንቲን የሚል ስም ያወጣላት፡፡ «ፋንቲን» ማለት ውሃ ወይም ምንጭ እንደማለት ነው፡፡

ስለዚህች ሴት ታሪክ ከዚህ ይበልጥ የሚያውቅ ስለሌለ ስላለፈው ታሪክዋ ከዚህ ይበልጥ መናገር አይቻልም፡፡ ሆኖም ፋንቲን ወደዚህች ዓለም ስትቃይ የመጣች በዚህ ዓይነት ነበር ብሎ ለማጠቃለል ይቻላል፡፡ ወደኋላ እንደተደረሰበት ደግሞ አሥር ዓመት ገደማ ሲሆናት ከከተማ ወጣ ብሎ ወደሚገኝ መንደር ሥራ ፍለጋ ትሄዳለች፡፡ በአሥራአምስት ዓመትዋ አሁንም ሥራ ፍለጋ ወደ ፓሪስ ከተማ ትመጣለች፡፡

በመጨረሻ ጥርሶችዋ ታዩ፤ እንደወተት የነጡ ነበሩ፡፡ ሌላ ቢጠቁ የእንጨት መፋቂያ አላጣችም ማለት ነው፡፡ ስታገባ የተሰጣት ሳይሆን አይቀርም የሚያማምሩ ጌጣጌጦች አንገትዋ ላይ አስራለች፡፡ ወይም ደግሞ ሥራ ብጤ አግኝታ ትንሽ ከሠራች በኋላ፤ የገዛቻቸው ይሆናሉ፡፡ ሴት ናትና ማጌጥ አይቀርም፡፡ እርስዋም እንደ ዓቅምዋ ለመኖር ፈልጋ ሥራ ይዛ ነበር ማለት ነው፡፡ ለመኖር ሆድ እንጀራ እንደሚርበው ሁሉ ልብም ፍቅር ይርበዋልና ልጅዋን እንደዚያ የምታይበት የፍቅር ረሃብዋን ለማርካት ነበር፡፡

ያ ስሜት ለሕፃንዋ የእናት ፍቅር ሲሆን ለእናትዮዋ ግን የስሜት

መንገፊል ነበር፡፡ እናትና ልጅ ከተቀመጡበት አትራቢያ የሚተላለፉ መንገደኞችና ተማሪዎች ቁጥር እጅግ ብዙ ነበር፡፡ ሕፃን ሆና ሕፃን የታቀፈችዋን ሴት ሁሉም አይቶ አለፋት እንጂ ከመጠጡና የቆጠራት አልነበረም፡፡

የሕፃንዋ አባት ልጅቱ እንደተወለደች ሚስቱንና ልጁን ጥሎ ከአገ[ር] ይጠፋል፡፡ አባት አንዴ ቤተሰቡን ጥሎ ከሄደ መመለስ ያጠራጥራል፡፡ ይህም በመሆኑ ልጅትዋ በብቸኝነት ዓለም ውስጥ እየዋገተች ስለነበር ተስፋ ከሚፈጥረው ደስታ ርቃለች፡፡ በአንድ ወቅት ተሳሳተች እንጂ በአፈጣጠርዋ ገራምና ትምክህት የተለየት ለመሆን ገጽታዋ ይመሰክራል፡፡ በፊትዋ ገጽታ ላይ የሚነበበው ገራምነትዋ ብቻ አልነበረም፡፡ ተስ[ፋ] መቁረጥዋን፣ ቀባሪና ጠዋሪ የሌላት መሆንዋንና ከከባድ ችግር ውስ[ጥ] መዘፈቅዋንም ያሳያል፡፡ ሆኖም ፋንቲን ቆራጥና ጠንካራ ሴት ነበረች፡፡ ወ[ደ] ትውልድ አገርዋ የመመለስ አሳብ ነበራት፡፡ ምናልባት ከእዚያ ከሄደ[ች] ድንገት የሚያውቋት ሰው ይኖርና ሥራ ይሰጠኝ ይሆናል የሚል እምነ[ት] አድሮባታል፡፡ ነገር ግን የፈጸመችውን ስህተት መደበቅ ስለነበረባት ልብ[ዋ] በዚህን ቢቆስልም አሳብዋን ለመፈጸም ቆረጠች፡፡ በሃያ ሁለት ዓመ[ትዋ] ሕፃን ልጅ አዝላ ከፓሪስ ከተማ ወጣች፡፡ የእናትና ልጅን ሁናቴ ከዚ[ያ] ተቀምጠው ለተመለከተ እጅግ ያሳዝናሉ፡፡ እናት በዚህች ዓለም ውስ[ጥ] ከልጅዋ በስተቀር ሌላ ሀብት አልነበራትም፡፡ ሕፃንዋም ከእናትዋ ሌላ ምን[ም] ነገር የላትም፡፡ ፋንቲን በደከመ አቅምዋ ለልጅዋ በማዘን መንገድ ሲሄ[ዱ] ታዝላታለች፣ ሲቀመጡ ትታቀፋታለች፡፡ በሽታዋ ሲጠናባት አልፎ አል[ፎ] ያስላታል፡፡

ተስዮት ላይ የፀሐይ ግለትን ለማሳለፍ ጥቂት ካረፉ በኋላ ጉዞአቸው[ን] ይቀጥላሉ፡፡ በፀሐይ ቁልቁል ስትል አሁን ከነበሩት በመድረሳቸውና በጣ[ም] ስለደከማቸው ነበር ከዚያ ያረፉት፡፡

እነዚያ ሁለት ልጆች ከጋሪው ወፍራም ሰንሰለት ላይ ቁጭ ብለ[ው] ደስ ብሎአቸው ሲጫወቱ በማየትዋ ፋንቲን ከአሳብ ባሕር ውስጥ ትዘፈቃለ[ች]

ልጆቹ ፊት ላይ ደስታ ይነበባል፡፡ ይህም ያ የተባረከና የተቀ[ደሰ] ሥፍራ እንደሆነ አሳመናት፡፡ ሆቴል ቤቱም በረከት ያልተለየውና መን[ፈስ] ቅዱስ የቀረበው ለመሆኑ ከልጆቹ ሁኔታ ገመተች፡፡ ሁለቱ ልጆች በእርግጥ ተደሳቾች ነበሩ፡፡ ልጆቹ ላይ አፈጠጠች፤ አደነቀቻቸው፡፡ ስለዚህ ነው የ[ፊ]... ብለን እንደገለጽነው «ደስ የሚሉ ልጆች ነው ያለዎት እሜቴ» በማ[ለት] ለመናገር የደፈረችው፡፡

የሁለቱ ልጆች እናት ቀና ብላ ካየቻት በኋላ ስለለጠችው አስተያ[የት] ታመሰግናታለች፡፡ ልጅ የታቀፈችው ልጅ ከሴትዮዋ ምግብ ቤት በ[ር]



ስለነበር የተቀመጠችው ሁለቱ ሴቶች ጨዋታ ይጀምራሉ፡፡

«መዳም ቴናድዬ እባላለሁ» አለች የሁለቱ ሴቶች ልጆች እናት፡፡ «ሆቴል ቤቱ የባለቤቴና የእኔ ነው፡፡»

መዳም ቴናድዬ ሸበት ጣል ጣል ያደረገባትና እንደ ወታደር ሚስት አንገትዋን የደፋች ስትሆን ጠባየ-ብልሹ ሴት ትመስላለች፡፡ ወንዳወንድ ብጤ ሆና ሰውነትዋ ደልዳላ ነው፡፡ ለረጅም ጊዜ ሆቴል ቤት ውስጥ ከገባና ከወጣ ሰው ጋር መጫጫህና ከወዲያ ወዲህ መሯሯጥ ይህን የመሰለ ባህርይ ሊያሰጥ ይችላል፡፡ ሸበት ቢወራትም በእድሜ እስከዚህም የገፋች አልነበረችም፡፡ ከሰላሣ ዓመት ብዙም አታልፍም፡፡ ሕፃን ልጅ ታቅፋ ኩምሽሽ ብላ ከተቀመጠችው እናት አጠገብ የቆመችውና እንደ ነጋዴ የፈረጠመና ደልዳላ ሰውነት ያላት ቴናድዬ ቀና ብለው ሲያዩዋት ትከብዳለች፡፡ ቁጭ ያለችዋ ሴት «እኔና እርስዎ አሁን እኩል ቁመን እንሂዳለን» ብላ ሳታስብ አልቀረችም፡፡

አንዱ ቁጭ ብሎ ሌላው ከአጠገቡ ቆሞ ቁልቁል እያየ ሲያፈጥ ትንሽ ማስፈራቱ አይቀርም፤ ያውም ግዙፍና ጠንካራ ብጤ ሰው ሲሆን፡፡ ለማንኛውም መንገደኛዋ ሴት ታሪኳ ውስጥ ትንሽ ቅመም እየጨመረች አወራቻት፡፡ በታሪክዋም ሥራ እንደነበራትና ባልዋ እንደሞተባት ተናገረች፡፡ ፓሪስ ከተማ ውስጥ ሥራ ልታገኝ ስላልቻለች ትውልድ አገርዋ ውስጥ እድልዋን ለመሞከር እየሄደች መሆንዋን ገለጸች፡፡ ከፓሪስ ከተማ ልጅዋን አዝላ የተነሳችው ገና ጎሕ ሲቀድ በእግር ጉዞ መሆኑንና አሁን በጣም ስለደከማት ለማረፍ ከበረንዳው ጥግ ሥር ቁጭ ማለትዋን፣ መንገድ ላይ ድካሙ ሲጠናባት ልጅዋ በእግርዋ ጥቂት መንገዋን ግን እጅግ በጣም ለአጭር ርቀት መሆኑን ከአስረዳች በኋላ ይህም በመሆኑ ሕፃንዋ በጣም ስለደከማት እንቅልፍ እንደወሰዳት ተናገረች፡፡

እናት ይህን እንደተናገረች የልጅዋን ጉንጭ ምጥጥ አድርጋ ትስማለች፡፡ በዚህ ጊዜ ሕፃንዋ ስለተቀሰቀሰች እነዚያ የሚያምሩ ዓይኖችዋን ገለጠች፡፡ ዓይኖችዋን ስትገልጥ ምን አየች? ምንም፡፡ የሁለት ዓመት ሕፃን ምንስ ታያለች? ግን እኮ እንዳንዴ ከስተር! እንዳንዴም ቀጣ በማለት ሕፃናት የማያዩት ነገር የለም፡፡ ያ ምስጢሩ ያልታወቀ ዓይን አይደለም ገራምነታቸውን የሚያሳየው! ምናልባት እኮ እነሱ መላእክ እኛ ግን ሰዎች እንደሆንን ይታያቸው ይሆናል፡፡

እናትዮዋ ብትቆጣም ሕፃንዋ መሳቅዋን ቀጠለች፡፡ ከእናትዮዋ ክንድ አምልጣ መሬት ወረደች፡፡ ወዲያው ከጋሪው ስር ይጫወቱ ወደነበሩት ሁለት ልጆች ሮጠች፡፡ ምን እንዳለች ሳይታወቅ ብቻ በመንተባተብ አንድ ነገር ተናገረች፡፡

መዳም ቴናድዬ «አብራችሁ ተጫወቱ» አለች።

በዚያ ዕድሜ መተዋወቅና መግባባት በጣም ቀላል ነው። የመ ቴናድዬ ልጆች አፈር እየፈጩና ጉድጓድ እየቆፈሩ በመጫወት ከ መጤዋ ሕፃን ጋር ደስ ብሎአቸው ይጫወቱ ጀመር።

አዲስዋ ሕፃንም ተግባቢና ተጫዋች ልጅ ነበረች። የእናትዋ ደ በሕፃንዋ ላይ ተንጸባርቆአል። ስንጥር አንስታ ለገንዘብ መቅበሪያ የሚ ጉድጓድ መቆፈር ጀመረች። የመቃብር ቆፋሪን ሥራ ሕፃናት ሲሠሩት ይላል።

ሁለቱ ሴቶች ጨዋታቸውን ቀጠሉ።

«ልጅሽን ማን ብለሽ ነው የምትጠሪያት?»

«ኮሴት።»

«ስንት ዓመት ሆናት?»

«ወደ ሦስት እየተጠጋች ነው።»

«ከትልቅዋ ልጄ ጋር እኩል ናት ማለት ነዋ!»

ሦስቱ ልጆች ደስ ብሎአቸው አብረው ሲጫወቱ አንድ አስደናቂ ነ ይሆናል። ትልቅ ትል ከሚቆፍሩት ጉድጓድ ውስጥ ወጣ። ልጆቹ በ ደነገጡ። በፍርሃት ቀና ሲሉ የሦስቱም ግምባር ተጋጨ። ጭንቅላታቸውን ሳያላቅቁ ዝም ብለው ትሉን በመገረም ተመለከቱ።

«እናንተ ልጆች ምን ሆናችሁ?» ብላ መዳም ቴናድዬ ጠየቀች። «ልጆች እኮ ሲተዋወቁ ጊዜ አይወስድባቸውም! እያቸው እስቲ! ሦስቱ ከአንድ እናት እንጀት የወጡ አይመስሉም» በማለት መዳም ቴናድዬ ቀ ተናገረች።

የሴትዮዋ አነጋገር በተጠንቶት ላይ የነበረው የሴላይቱ እናት እ መዘርገፍ ምክንያት ሆነ። ፋንቲን የመዳም ቴናድዬን እጅ ያዘች።

«ልጄን ያሳድጉልኛል?»

«ምን አልሽ!»

«ልጄን ያሳድጉልኛል?»

«ትንሽ ነገሩን ማብላላት አያስፈልግ ብለሽ!»

«በወር ስድስት ፍራንክ እከፍልዎታለሁ።»

ከቤት ውስጥ ጎርነን ያለ የወንድ ድምፅ ተሰማ።

«በሰባት ፍራንክ በታች አይሆንም፤ ደግሞም የስድስት ወር ክ



በቅድሚያ ነው የሚከፈለው። ስድስት ጊዜ ሰባት አርባ ሁለት ፍራንክ መሆኑ ነው።»

«እከፍላለሁ» አለች የካዜት እናት።

«አንዳንድ ነገሮችን ለማሟላት አንድ አሥራ አምስት ፍራንክ በተጨማሪ ያስፈልጋል» አለ ቀጠለና ሰውዬው።

«እንግዲህ በድምሩ አምሳ ሰባት ፍራንክ መሆኑ ነው» አለች መዳም ቴናድዬ።

«እከፍላለሁ» አለች ደሃዋ እናት። «አሁን በእጄ ያለው ሰማንያ ፍራንክ ነው። ቀሪው ገንዘብ እንደምንም ብሎ አገሬ ያስገባኛል። ከዚያ ደግሞ ሥራ አላጣም። ወዲያው ትንሽ ገንዘብ እንዳፈራሁ ተመልሼ መጥቼ ልጄን እወስዳታለሁ።»

የሰውዬው ድምፅ እንደገና ተሰማ።

«ለመሆኑ የሌሊት ልብስ አላት?»

«ባለቤቴ ነው» አለች ማዳም ቴናድዬ።

«በሚገባ፤ ደግሞ ለእርስዎ ያልሆንኩ። ባለቤትዎ እንደሆኑ እኔም ጠርጥሬአለሁ። እኔው ፈትዬ ያሠራሁላት ወፍራም ልብስ አላት። የሌሊት ብቻ ሳይሆን ቀን ቀን የምትለብሰውም ከለበሰችው ሌላ ሁለት ቀሚስ አላት።»

«እንግዲያው ልብሶችዋን ትተሽ ነው የምትሄጂው» አለ ሰውዬው።

«ይዤው-ማ አልሄድም» አለች እናት። «ልጄን ራቁትዋን ጥያት ብሄድ ሰው ጉድ አይልም።»

ሰውዬው ከነበረበት ወደ ውጭ ብቅ አለ።

«ይሄ ጥሩ ነው» ሲል ተናገረ ዝቅ ባለ ድምፅ።

በዚህ ተስማሙ። የካዜት እናት ያን እለት እዚያው አደረች። ገንዘቡን ከፈለች። የልጅትዋንም ልብስ ሰጠች። በማግስቱ የቀራትን ጨርቅ ቋጥራና በቶሎ እንደምትመለስ ቃል ገብታ የእግር ጉዞዋን ቀጠለች። ምንም እንኳን በጥሞና የተፈጸመ ስምምነት ቢሆንም የወለደቻትን ልጅ ጥላ ለምትሄድ እናት ቀላል ውሳኔ አልነበረም። እንጀትን ከሁለት የሚከፍል ዓይነት ውሳኔ ነው።

የእነማዳም ቴናድዬ ጎረቤት ፋንቲንን መንገድ ታያታለች። ሴትዮዋ «እንዴት አደራችሁ» ለማለት ከእነቴናድዬ ቤት ጎራ ትላለች።

«ይገርማችኋል፤ አሁን አንዲት ሴት መንገድ አይቼ ነው የመጣሁት።

ሴትዮዋ ስታሳዝነኝ! በልቅሶ ብዛት ልብዋ የፈረጠ እስኪመስል ነው እያለቀሰች የሄደችው::»

የኮዜት እናት እንደ ሄደች ባል ሚስቱን እንዲህ አላት::

«ይሄ ገንዘብ እኮ ከሰማይ እንደወረደ ነው የሚቆጠረው:: ነገ እኮ ለማዘጋጃ ቤት 110 ፍራንክ እንድንከፍል የታዘዘበት የመጨረሻው ቀን ስለሆነ ለዚያ ማሟያ ይሆነናል:: '50 ፍራንክ ጎደለብኝ፤ ከየት አባቴ አመጣለሁ' እያልኩ ስጨነቅ ነበር:: በልጆቿ ሰበብ ደህና ይህችን ሴት አጠመድሽልኝ::»

«ያውም ሳይታወቅብኝ» አለች ሴትዮዋ::

# ፫

ወጥመድ ውስጥ የገባ አይጥ ማምለጫ አጥቶ ይቅበዘበዛል:: ከድመት ጥፍር ውስጥ የገባ ፍጡር ግን ይበልጥ ይፈነቃል::

ማዳምና ሚስተር ቴናድዬ ምን ዓይነት ሰዎች ይሆኑ?

ምድባቸው እውቀት ኖሯቸው ግን ጊዜ ከጣላቸው ሳይሆን የተናቁ ሆነው ጊዜ ካነሳቸው ሰዎች ውስጥ ነበር:: ጊዜ ያነሳቸው ሰዎች ጥፋት ሲፈጽሙ የሠርቶ አደሩ ትጋት ወይም የቡርዥው ክብር የተጐናጸፉ ባይሆኑም ስህተታቸው ጊዜ ከጣላቸው ሰዎች ላይ ተደፍድፎ እነርሱ ከጥፋቱ ነፃ ይሆናሉ::

ይህም በመሆኑ ባልና ሚስት መደባቸው ከተናቁ ሰዎች መካከል ቢሆንም ጊዜ ስለሰጣቸው ብቻ እንደ ትልልቅ ሰዎች ይከበራሉ:: ሴትዮዋ ጨካኝ፤ ሰውዬው በዋል-ፈሰስ ዓይነት ሰዎች ነበሩ:: ሁለቱም ትንሽ ቀዳዳ ካገኙ ተንኮል ከመሥራት አይቆጠቡም:: እንደ ትል ከብርሃን ወደ ጨለማ፤ እንደ አባያ በሬ ወደፊት ከመራመድ ወደኋላ ማፈግፈግ፤ እንደ እባብ ከቀና አስተሳሰብ ተንኮል ወደ መሸረብ፤ ከሰፊው ጠባብ መንገድን የሚመርጡ ዓይነት ሰዎች ናቸው::

የሚገርመው ግን ክፋት፤ ተንኮልና ምቀኝነት ለኑሮ መሳካት ዋስትና ሊሆን ስለማይችል እነዚህ ሰዎች በሆቴል ቤታቸው ብዙም አልተጠቀሙም::

ፋንቲንን ያመሰግኑና ላያስቡት በድንገት ሃምሣ ሰባት ፍራንክ



አግኝተዋል:: ይህን ገንዘብ በማግኘታቸው ሆቴል ቤታቸው ከመታሸግ ዳነ:: ግን አሁንም ቢሆን በሚቀጥለው ወር ተጨማሪ ገንዘብ ያስፈልጋቸው ስለነበር ሴትዮዋ የኮዜትን ጋቢና ቀሚሶች ወደ ገበያ ወስዳ በስልሣ ፍራንክ ሸጠቻቸው:: ገንዘቡ ሲያልቅ ኮዜትን ለነፍሳችን ብለው ያስጠግዋት እንጂ ጥቅም እንዳገኙባት ረስተው በጣም ጨከኑባት:: የራስዋ የሆኑ ልብሶች ተሸጠው የተበጫጨቁትን የልጆቻቸው ውራጅ አለበሱዋት:: ለውሻ እንደሚሰጥ አጥንት ከበላተኛ የወዳደቀ ትርፍራፊ አበልዋት:: ምድብዋ በር ላይ ተኝቶ ዓይን ዓይን ከሚያይ ውሻና ከተመጋቢ እግር ስር ድምፅ እያሰማ ከሚሄድ ድመት ጋር ሆነ:: ምግብ እንደ ውሻና ድመት በገበቴ መሣይ ነገር መሬት ተጣለላት::

እናትዋ አገርዋ ከገባች በኋላ ከእዚህ ግባ የማይባል ሥራ አገኘች:: በየወሩ ደብዳቤ ለእነሚስተር ቴናድዬ ጻፈችላቸው:: በደብዳቤዋ ከልጅዋ ደኅንነት በስተቀር ሌላ የምትጠይቀው ነገር አልነበራትም:: ባልና ሚስት የመልስ ደብዳቤ ሲልኩ ኮዜት ተመችቶአት እንደምትኖርና ጤናዋም ደህና መሆኑን ገልጸው ነበር የሚጽፉላት::

አንዳንድ ልቦች በአንድ ጎናቸው ጥላቻን ካላቀፉ ፍቅር ብቻውን መንተራስ የማይችሉ አሉ:: መዳም ቴናድዬ የራስዋን ልጆች በጣም ትወዳለች:: የልጆችዋ ፍቅር አዲስዋን ልጅ እጅግ እንድትጠላ አደረጋት:: ኮዜት ያለ አግባብ ስትነቀፍ፤ ስትገረፍ፤ ስትሰደብ፤ ስትመናጨቅና ስትጠላ እኩዮችዋ የሆኑ ሌሎቹ ሁለት ልጆች ሲታቀፉ፤ አሽሩሩ ሲባሉ፤ የማይገባቸውን ምስጋና ሲያገኙ በማየትዋ ነገሩ ሊገባት አልቻለም:: የሰው ልጅ ጭካኔ፤ የዚህ ዓለም ውጣ ውረድ፤ የእግዚአብሔር ሽረትና ምህረት ምን እንደሆኑ ለማወቅ እድሜዋ አልፈቀደላትም::

ሴትዮዋ ትጨክንባታለች:: ኢፖኒንና አዜልማም ይጨክኑባታል:: ምናልባት የጭካኔው መጠን ይለያይ ይሆናል እንጂ በዚያ እድሜ ልጆች ቤተሰቦቻቸው የሚፈጽሙትን ነው የሚከተሉት::

ዓመት አለፈ፤ ሌላውም ተደገመ::

የሰፈር ሰዎች ምን ብለው ያወሩ ጀመር፤ «እነመዳም ቴናድዬ ምን ዓይነት ርህሩህና ደግ ቢሆኑ ነው እባካችሁ:: እነርሱ ለራሳቸው ምስኪኖች ሆነው መጠጊያ የሌላትንና እናትዋ የጣለቻትን ልጅ ያሳድጋሉ::»

የገዛ እናት ልጅዋን የረሳች መሰላቸው::

ከዓመት እስከ ዓመት ቁመትዋ እየጨመረ ሲሄድ መከራዋና ስቃይዋም እንዲሁ ጨመረ::

ክቤት ሕፃን ሆና ሳለ የሁለቱ ልጆች ጥፋት ማስተባበያ ነበረች፡፡ እያደገች ስትሄድ ማለት አምስት ዓመት ሳይሞላት የቤቱ አሽከር ሆነች፡፡

ክቤት ትላላካለች፣ ቤት ትጠርጋለች፣ ግቢ ታጸዳለች፣ እቃ ታጥባለች፣ ከባድ ነገር ትሸከማለች፡፡ እናትዋ በየወሩ የምትከፍለውን ገንዘብ ባጎደለች ቁጥር ልጅትዋ የምትሸከመው ሸክም እየከበደ ይሄዳል፡፡ እናትዋ የጥቂት ወሮችን ክፍያ አልላከችም፡፡

እናት ከሦስት ዓመት በኋላ ወደ ሞንትፌርሜ ከተማ ብትመለስና ልጅዋን ብታያት አታውቃትም፡፡ ያኔ ጥላት ስትሄድ ድምቡሽቡሽ ብላ ንከሱኝ፣ ግመጡኝ ትል የነበረችው ልጅ ጠቁራና መንምና አጥንትዋ ገጥጦ፣ ፊትዋ ገርጥቶ ሌላ ልጅ መስላለች፡፡ «እደለ-ቢስ! ገዳፋ» እያሉ ነው ባልና ሚስት የሚጠሩዋት፡፡

እድልዋ ዝምተኛ እንድትሆን፣ ችግርዋ ፋንጋ እንድትመስል አድርጓታል፡፡ ዓይኖችዋ ቢጎደጉዱም ከቦታቸው አልጠፉም፣ ሲያዩዋቸው ያስፈራሉ፡፡ ስቃይ እንዳንገላበባቸው ያስታውቃሉ፡፡ ትላልቅ ስለነበሩ ያዘሉትም የስቃይ መጠን ትልቅ ነበር፡፡

ዓይኖችዋ እንባ አቅርረው፣ በክረምት ቡትቶ ለብሳ አፈር ላይ ስትተኛና በበጋ ደባደቦ ለብሳ በጠራራ ፀሐይ ከቁመትዋ የሚበልጥ መጥረጊያ ይዛ ደጃፍ ስትጠርግ ማየት ልብ ላለው የሚዘገንን ትርኢት ነበር፡፡ ሆኖም ሰዎች «እድለቢስ.... ገዳፋ... እቡይ» እያሉ ነበር የሚጠሩዋት፡፡

ጠዋት ጠዋት እየተባችና እየፈራች ሰውነትዋ ተንቀጥቅጦ በቅጡ ሳይነጋ ነበር የምትነሳው፡፡ ከሰፈር የምታመጣው ነገር ካለ የሰፈር ሰው ሳይነሳ ትሄድና እስኪነሱ ትጠብቃለች፡፡ከገበያም የምትገዛው እቃ ካለ ገበያተኞች እቃቸውን ሳያወጡ እርስዋ ቀድማ ትገኛለች፡፡

❀❀❀

## ምዕራፍ አራት

## ደጉ ሰው

የዚያች ምስኪን ልጅ እናት ምን ሆነች? ሞንትፌርሜ ውስጥ ይኖሩ የነበሩ ሰዎች ልጅዋን ከድታ እንደጠፋች ሲናገሩ ሰምተናል፡፡ የት ነው ያለችው? ምን እየሠራች ነው?



ክቤትን ከነማዳም ቴናድዬ ቤት ትታ ከሄደች በኋላ ትውልድ አገርዋ በደህና ደርሳለች፡፡ ከአሁን በፊት እንደተጠቀሰው ዘመኑ 1818 ዓ.ም. ነበር፡፡ ፋንቲን ወደ ትውልድ አገርዋ የተመለሰችው አገሩን ለቅቃ በወጣች በአሥራ ሁለተኛ ዓመትዋ ነበር፡፡ አገሩ በጣም ተለዋውጦ ነው ያገኘችው፡፡ የእርስዋ ኑሮ እያቆለቆለ ሲሄድ የትውልድ አገርዋ ከተማ በጣም እያደገና እየተሻሻለ ሄዷል፡፡ በመጨረሻዎቹ ሁለት ዓመታት በተለይ ትልቅ መሻሻል ተገኝቶ አነስተኛ ኢንዱስትሪዎች ተቋቁመዋል፡፡

በዚያ አገር ፋብሪካ ውስጥ ተመርተው የሚወጡ ዕቃዎች ዋጋ እጅግ የናረ ነበር፡፡ ነገር ግን ፋንቲን ወደ አገርዋ ስትመለስ ያ ሁናቴ ተለውጦ ነው የደረሰችው፡፡ አንድ ያልታወቀ ሰው በ1815 ዓ.ም. መጨረሻ ገደማ መጥቶ አስደናቂ የሆነ የፈጠራ ሥራ በመሥራቱ የፋብሪካ ውጤቶች ዋጋ ዝቅ ይላል፡፡

ሦስት ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ሰውዬው ከመጠን በላይ ሀብታም ይሆናል፡፡ ፋብሪካው ውስጥ ይሠሩ የነበሩ ሰዎች ደግሞ ጥሩ ደመወዝ ስለተከፈላቸው እነሱም የተሻሻለ ኑሮ መኖር ቻሉ፡፡ ሰውዬው ማን እንደሆነና ከየት እንደመጣ ግን ማንም አያውቅም፡፡ ወደ ከተማው ሲመጣ ምንም ገንዘብ ይዞ እንዳልመጣ ሁሉም የሚያውቀው ነው፡፡ ግን እርሱ በወጠነው የፈጠራ አሳብ እርሱ ብቻ ሳይሆን አገሩ ሁሉ ከበረበት፡፡ ወደዚያ ሲመጣ አለባበሱም ሆነ አነጋገሩ የጭቁን ሰው ነበር፡፡ በታኅሣሥ ወር ለዓይን ያዝ ሲያደርግ ወደ ከተማው ሲገባ የለበሰው ልብስ የተበጫጨቀ እግሩና እጁ በሥራ ብዛት የሻከረ ሲሆን በአንድ እጁ ምርኩዝ መሳይ ነገር ይዞ፣ በሌላ እጁ በጨርቅ የተጠቀለለ ነገር አንጠልጥሎ ነበር፡፡ በእለቱ እርሱ ወደ ከተማው ሲገባ ሰፈር ውስጥ የእሳት ቃጠሎ ተነስቶ ስለነበር ሰውዬው በቀጥታ ወደ እሳት ቃጠሎው ይሄዳል፡፡ ልክ እርሱ ሲደርስ ሁለት ትንንሽ ልጆች በእሳቱ ተከበው ያያል፡፡ ዘሎ ገብቶ ይዞአቸው ይወጣል፡፡ ልጆቹ የባለሥልጣን ልጆች ነበሩ፡፡ በዚያ ግርግር የከተማው ሹሞች የመታወቂያ ወረቀት ሳይጠይቁት ከሕዝብ ጋር አብሮ ይቀላቀላል፡፡ እንኳን የመታወቂያ ወረቀት ሊጠየቅ ስለፈጸመው በጎ ተግባር ሰው ሁሉ ከብቦ ያመሰግነዋል፡፡ ከዚያች ሰዓት ጀምሮ ሁሉም ሰው «አባባ ደጉ ማንደላይን» እያለ ጠራው፡፡

ዕድሜው በግምት ሃምሳ ይሆናል፡፡ አሳብ ስለሚያጠቃው ዘወትር ትክዝ ከማለቱ በስተቀር ስለዚህ ሰው ከዚህ ይበልጥ በአሁኑ ሰዓት ማውራት አይቻልም፡፡ ብቻ እርሱ በፈጠረው ጥበብ ሳቢያ በብዛት ተሠርቶ ለሚወጣው የፋብሪካ ውጤት ምስጋና ይግባውና የብዙ ሰው ሕይወት ተሻሻለ፡፡ ከተማዋ የነጋዴዎች መናኸሪያ ሆነች፡፡ እቃው ከአገር ውጭ ወደ እስፓኝ በብዛት ተወሰደ፡፡ የእቃው ዓይነት እንግሊዝና ጀርመን አገር ተመርተው ከሚወጡት

ተመሳሳይነት ካላቸው እቃዎች የተሻለ ሆኖ በመገኘቱ ተወዳጅነትን አተረፈ:: ስለዚህ ገቢያው ደራ፤ የሚገኘውም ጥቅም እጅግ ብዙ ስለሆነ አባባ ማንደላይን በሁለተኛው ዓመት ሌላ መጠነኛ ፋብሪካ ከፈተ:: ፋብሪካው ውስጥ አንደኛው ክፍል ውስጥ ሴቶች ብቻ የተሰማሩበት ነበር:: ከእዚያ ከተማ ሥራ ያጣ ሁሉ ከእነዚህ ሁለት ፋብሪካዎች ውስጥ በደህና ደመወዝ ሥራ በቀላሉ ማግኘት ቻለ:: አባባ ማንደላይን ከመምጣቱ በፊት ብዙ ሰው ሥራ ስላልነበረው ከተማይቱ ውስጥ ብዙም እንቅስቃሴ አልነበረም:: አሁን ግን ሁሉም በየፊናው መፍጨርጨሪያ መንገድ ስለተከፈተለት ከተማው ተንቀሳቀሰ:: የኢኮኖሚ መንቀሳቀስ የተፈለገው ነገር ሁሉ የትም አስገኘ:: ሥራ መፍታትና ችግር ከከተማው ተወገዱ:: እያንዳንዱ ነዋሪ መጠነኛ የሆነ ገቢ ስለአገኘ ሁሉም እንደአቅሙ፤ በደረጃው ደስ ብሎት ደኖር ጀመር::

ነገር ግን አባባ ማንደላይን ለሁሉም ሥራ ቢያስገኝም ሥራ ለሰጠው ሁሉ «ታማኝና እውነተኛ ሰው መሆን አለባችሁ» እያለ ያስጠነቅቅ ነበር::

ተደጋግሞ እንደተገለጸው በዚህ አጋጣሚ የአባባ ማንደላይን ሀብት ተትረፈረፈ:: የሚገርመው ግን ይህ ሰው ለሀብት ይህን ያህል ደንታ አልነበረውም:: ከሀብቱ ይልቅ ስለሌሎች ሰዎች ደኅንነት እጅግ ያስባል፤ ይጨነቃል:: ለራሱ ግን ብዙም ግድ አልነበረውም:: በ1920 ዓ.ም. ባንክ ውስጥ ስድስት መቶ ሰላሳ ሺህ ፍራንክ ነበረው:: በዚያው ዓመት ደግሞ ለከተማው እድገትና ለተቸገረ ድሃ ያወጣው ገንዘብ ወደ አንድ ሚሊዮን ፍራንክ ገደማ ነበር::

ከተማው ውስጥ የነበረው ሆስፒታል የተሟላ ክፍልና አልጋ ስላልነበረው የሕሙማን ማስተኛ አሥር ተጨማሪ አልጋዎች እንዲገዙ አደረገ:: ከተማው የላይኛውና የታችኛው ተብሎ ከሁለት የተከፈለ ሲሆን እርሱ ይኖርበት የነበረው የታችኛው ከተማ ብዙ የጎደለው ነገር ነበር:: አንድ ትምህርት ቤት ብቻ ነበር ያለው:: እርሱም ቢሆን ሊፈርስ ምንም ያህል አልቀረው:: ስለዚህ ሁለት አዳዲስ ትምህርት ቤቶችን አሠራ:: አንደኛው ትምህርት ቤት ለሴቶች ሌላው ለወንዶች ተመደበ:: ከግሉ ወጪ አራት አዳዲስ አስተማሪዎችን ቀጥሮ መንግሥት ከሚከፍለው የአስተማሪ ደመወዝ እጥፍ ከፈላቸው:: ይህን ያየ ጎረቤቱ ስለሠራው ሥራ አድንቆ ሲናገር «ነርስና አስተማሪ እኮ ምርጥ የአገር ገንዘቦች ናቸው» አለ ይባላል:: ፈረንሣይ አገር እጅግ የታወቀ ጠዋሪና ደጋፊ ለሌላቸው የሚሆን ትልቅ ቤትም አሠራ:: ፋብሪካው መሃል ከተማ ውስጥ ስለነበር በፋብሪካው ጭስ ሰበብ የሰፈሩ ነዋሪዎች ስለተጎዱ በነፃ መድኃኒት የሚወሰዱበት የመድኃኒት ቤት ከፈተላቸው::



በ1817 ዓ.ም. ይህ ሰው የሠራው በጎ ምግባር በመላ ፈረንሣይ በመሰማቱ በዚያን ጊዜ የነበረው ንጉሥ አባባ ማንደላይንን የከተማው ከንቲባ አድርጎ ሊሾመው ነው ተብሎ ተወራ:: ወሬው አሉባልታ ሆኖ አልቀረም:: ከጥቂት ቀናት በኋላ የአባባ ማንደላይን መሾም በጋዜጣ ታትሞ ወጣ:: አባባ ማንደላይን ግን ሹመቱን የማይበቀለው መሆኑን አስታወቀ::

ወደ ከተማው በገባ በአምስተኛው ዓመት ማለት በ1820 ዓ.ም. ደጉ ሰው ለሕዝብ ጥቅም ብሎ ያሠራው ነገር እጅግ በጣም የገነነ በመሆኑ የከተማው ነዋሪ ሁሉ እርሱ የከተማው ከንቲባ እንዲሆን ጥቆማው አስተጋባ:: ንጉሡ እንደገና ሾመው:: አሁንም ሹመቱን አልቀበልም አለ:: ግን የከተማው ፖሊስ አዛዥ «ሹመቱን እንዲቀበል በግድ መታዘዝ አለበት» ሲል አስታወቀ:: የከተማው ታላላቅ መኳንንትም ከቤቱ ድረስ ተሰብስበው መጥተው «ሹመቱን መቀበል አለብህ» አሉት:: የወዝ አደሮችም አሳብ ከዚህ የተለየ አልነበረም:: ሰው ሁሉ ሹመቱን እንዲቀበል ስለወተወተው በመጨረሻ እሺ ብሎ የከተማው ሹም ሆነ::

ሰው ሁሉ ሹመቱን እንዲቀበል የገፋፋው አንዲት የኑሮ ደረጃዋ ዝቅተኛ የሆነ አሮጊት ከሰፈር ሰፈር እየዞረች በቁጣ «ጥሩ ከንቲባ ማግኘት እኮ ጥሩ ነገር ነው፤ ደግ ሥራ የሚሠራ ሰው አይወድላችሁም?» እያለች ሕዝቡን በመቀስቀስዋ ነበር:: ብዙ ሕዝብ ካልበዛበት ከተማ ወሬ ስለማይደበቅ ይህች ሴት የምትለው ነገር በአጭር ጊዜ ከተማው ውስጥ ተሰራጨ:: ጊዜ እያለፈ ሲሄድ ግን ቁጥሩ አነስተኛ ቢሆንም የሚቃወም አልጠፋም::

መቼም የሕይወት እውነታ ነው፤ በራሳቸው ጥረትና ችሎታ ወይም በሌሎች ደግነት ሥልጣን ላይ የወጡ ሰዎች ተቃዋሚ አያጡም:: መሴይ ማንደላይንም ቢሆን ከዚህ ሊርቅ አይችልም:: ግን ተቃውሞው ብዙ ጊዜ አልቆየም:: እንዲያውም የሚገርመው ከተሾመ በኋላ በሕዝቡ ዘንድ ያለው አድናቆትና አክብሮት እየጨመረ ሄደ:: የተጣላን ያስታርቃል፤የታመመን ይጠይቃል፤ ከዚህ ዓለም በሞት የተለየውን ይቀብራል:: ሰውም በራሱ ፈቃድ ዳኛ አደረገው:: የዓለም ሕግ ልቡ ላይ የተጻፈ ይመስል የሚሰጠው ፍርድ የተወላገደ፤ የሚሰጠው ምክር የተጣመመ አልነበረም:: የነገርን ፊት ለፊት እንጂ ወደኋላ አያውቅም:: በዚህም የተነሣ ከስድስትና ሰባት ዓመት በኋላ ስሙ በነበረበት ክፍለ ሀገር ብቻ ሳይሆን በመላ ፈረንሣይ እጅግ ገነነ::

ነገር ግን በአንድ ሰው ብቻ ተጠምዶ ይያዛል:: ይህ ሰው አባባ ማንደላይን የሚያደርገውን ሁሉ ይቃወማል:: ሁልጊዜም ይጠራጠረዋል:: ስሜቱ ብቻ ሳይሆን መላ ሰውነቱ ማንደላይንን አይቀበልም::

ዘወትር መሴይ ማንደላይን በመንገድ ባለፈ ቁጥር ሰው ሁሉ በፍቅር